# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ልማት ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ልማቱ የአካባቢንና የህብረተሰቡን ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን ለማረጋገጥ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

*ታህሳስ 2005 ዓ.ም.*

አዲስ አበባ

**ማውጫ**


ክፍል አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረትና አሰራር ........ 1
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ፣ ራዕይ እና ሥልጣንና ተግባር; ........ 2
ዓላማ (Objective) ........ 2
ራዕይ (Vision) ........ 2
ሥልጣንና ተግባር ........ 2
የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ሀይል ........ 3
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 3
የኦዲቱ ዓላማ ........ 3
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫና የመመዘኛ መስፈርት ........ 4
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 4
የማዕድን ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ........ 6
የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ........ 6
የአካባቢ ማህበረሰብ ልማት ዩኒት ........ 6
ክፍል ሁለት ........ 7
ግኝቶች ........ 7
2.1 የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ በማልማት ስራ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 7
በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓትን በተመለከተ፤ ........ 7
ለዱር እንስሳት እና ለተፈጥሮ ደን ሀብት ጥበቃ በተከለሉ አካባቢዎች የማዕድን ፈቃድ የማይሰጥ መሆኑን በተመለከተ ........ 8
የማዕድን ቅኝት፣ የምርመራ እና የማምረት ፈቃዶች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜን በተመለከተ፤ ........ 10
ማዕድን ለማልማት ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በገቡት ውል መሰረት መስራታቸውን በተመለከተ፤ ........ 11
የሮያሊቲ፣ እና የመንግስት ነፃ የአክሲዮን ድርሻ ክፍያዎችን በተመለከተ፤ ........ 12
የማዕድን ፍቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች የአፈፃፀም ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ፤ ........ 14
በማዕድን ልማት ለሚሳተፉ አካላት ለልማቱ የሚያግዙ መሳሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከቀረጥ ነፃ የማስገባት መብትን በተመለከተ፤ ........ 15

2.2 የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎች ለማስወገድና ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፤ .......... 17

የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያን በተመለከተ፤ .......... 17

የማዕድን ፈቃድ ጠያቂዎች ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ማቅረብን በተመለከተ፤ .......... 17

ህብረተሰቡ ከማዕድን ልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓትን በተመለከተ፤ .......... 18

የአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ መመደቡን በተመለከተ፤ .......... 19

ለማዕድን ስራ ጤንነትና ደህንነት ደንብና መመሪያን በተመለከተ፤ .......... 20

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ልማት ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤ .......... 21

2.3 የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ .......... 22

የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን በተመለከተ፤ .......... 22

የካዳስተር ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ .......... 23

በባለፈቃዶች መያዝ የሚገባቸውን መረጃዎች በተመለከተ .......... 24

ክፍል ሦስት፡ .......... 25
መደምደሚያዎች .......... 25

ክፍል አራት፡ .......... 28
የማሻሻያ ሀሳቦች .......... 28

አባሪ 1 .......... 31
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) .......... 31

አባሪ 2 .......... 34
የሥራ ሂደት መግለጫ (Process discriptions) .......... 34
የማዕድን ፍለጋ/ምርመራ ሥራ ፈቃድ የሥራ ፍሰት .......... 34

የማዕድን ምርት ሥራ ፈቃድ የሥራ ፍሰት .......... 35

የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት .......... 36

የአካባቢ ማህበረሰብ ልማት ዩኒት .......... 37

አባሪ 3 .......... 38
በናሙና የተመረጡ ክልሎችና ወረዳዎች .......... 38

በናሙና የተመረጡ በማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ የተሰጣቸውና የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው ባለፈቃዶች ዝርዝር .......... 38

አባሪ 4 ... 39
በናሙና ከተመረጡት ባለፈቃዶች ዉስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ማዕድን ለማምረት ፈቃድ ለመስጠት የጠቀመጠውን የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ወይም መስፈርቶች አሟልተው ፈቃድ ስለመሰጠቱ መረጃ ያልቀረበላቸው ... 39

አባሪ 5 ... 41
ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርመራ ፈቃድ ወስደ. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ፈቃዳቸው በወቅቱ ለማሳደሳቸው ወይም ለመሰረዙ ማስረጃ ያልቀረበላቸው ባለፈቃዶች ዝርዝር ... 41

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የኢትዮጵያ የማዕድን ሃብት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሀብት እንደመሆኑ መጠን፣ መንግስት የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት የመጠበቅ ኃላፊነቱን ለመወጣት፣ ሃብቱ ብክነት በሌለበት ሁኔታ የሚለማበትንና ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥቅም የሚውልበትን ሁኔታ የሚያስፋፋ የህግ፤ የአስተዳደራዊ ሥርዓት እና ተቋማዊ ማዕቀፍ በማደራጀት የማዕድን ሀብቱ በጥቅም ላይ እንዲዉል ማድረግ አለበት፡፡ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ በእድሜ ከፕሪካምብሪያን (ከክርስቶስ ልደት በፊት) እስከ ቅርብ ዘመን ባሉት የአለቶች ቅንብር እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ይገለፃሉ፡፡ በኢትዮጵያ ያሉት የተለያዩ የአለቶች ቅንብር በዛ ላሉ ማዕድናት መፈጠር አመቺ በመሆናቸው የከበሩ ማዕድናት፤ ብርቅዬ ማዕድናት፤ ቤዝሜታልስ፤ የጌጣጌጥ፤ የኢንዱስትሪ፤ የግንባታ እና የኃይል ምንጭ ማዕድናት እንዲሁም ዳይሜንሽን ስቶንስ (Dimension stone) የመሳሰሉ የማዕድን ሀብቶች ይገኛሉ፡፡
2. እነዚህን ማዕድናት በጥቅም ላይ ለማዋል ግልጽ የሆነ የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ይህ ሥርዓትም የህዝብና የሀገሪቱን ሀብት በማስጠበቅ እና የህብረተሰቡ እና የአካባቢውን ደህንነት በሚያስጠብቅና በማይጎዳ ሁኔታ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረትና አሰራር

3. በኢትዮጵያ ውስጥ የማዕድን ሥራ በተለያየ አደረጃጀት ተዋቅሮ ሲካሄድ የነበረ ሲሆን፣ ክፍለ ኢኮኖሚው በ1963 ዓ.ም በወጣው የማዕድን አዋጅ ቁጥር 282 መሰረት የ1952 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ የንግድ ህግ መሰረት ማንኛውም ነጋዴ ተብሎ የተመዘገበ ሰው የብቻ የሆነ የማዕድን ማምረት የሚያስችል ፈቃድ እንዲያገኝ ተደርጎ ነበር፡፡ በ1967 ዓ.ም በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 39/67 የግል ኩባንያዎች እና ግለሰቦች በግንባታ ማዕድናት ምርመራና ማምረት ስራ ላይ እንዲሰማሩና ለብረት ነክ ማዕድናት የሚደረግ የምርመራና የማምረት ሥራ በመንግስትና በግል በሽርክና ብቻ የማምረት ሥራ እንዲሆን ገደብ ተጣለ፡፡
4. በ1968 ዓ.ም በስራና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሥር፣ ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ በማዕድን፣ ኃይል ምንጭ፣ ዉሃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር፣ ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ በማዕድንና ኃይል ምንጭ ሚኒስቴር፣ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥር ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ ከ1983 የመንግስት ለውጥ በኃላ ከማዕድን ምርመራና ማምረት ስራ ጋር የተያያዘዉን ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ሥጋት (risk) ለማሰተዳደርና ለመቋቋም በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ አዲስ የማዕድን አዋጅ በ1985 ዓ.ም እንዲሁም የማዕድን ደንብ

ደግሞ በ1986 ዓ.ም ወጥቷል፡፡ከመስከረም 1994 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የማዕድኑ ዘርፍ ራሱን ችሎ በማዕድን ሚኒስቴር ከጥቅምት 01 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥር እንደ አንድ ዘርፍ ተዋቅሮ እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ቆይቶ ነበር፡፡ በ2003 ዓ.ም በተደረገው የአስፈፃሚ አካላት የአደረጃጀት ለውጥ የማዕድን ዘርፉ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 እራሱን ችሎ ለብቻው በሚነስቴር ደረጃ የማዕድን ሚኒስቴር ተብሎ እንደገና እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ እነዚህ ህጎች የግሉ የኢኮኖሚ ዘርፍ በማዕድን ፍለጋና የማምረት ሥራ ላይ በሰፊው እንዲሳተፉ በር ከፍቷል፡፡ በዚህም መሰረት በዚሁ ዘርፍ ለመሰማራት ለጠየቁ ከ264 በላይ ለሚሆኑ የማዕድን ፍለጋና የማምረት ፈቃድ በማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤት ተሰጥቷል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ፣ ራዕይ እና ሥልጣንና ተግባር;

### ዓላማ (Objective)

5. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማዎች፡-

- መንግስት የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት ለመጠበቅ የተጣለበትን ኃላፊነት ተግባራዊ ማድረግ፣
- የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ማስፋፋት፤
- የኢትዮጵያውያንን የስራ ዕድል ማስፋፋትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማሳደግ፤
- በማዕድን ምርመራና ማምረት ሥራ የተሰማሩትን ባለሀብቶች የይዞታ ዋስትና ማረጋገጥ እና፤
- የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ሥርዓትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መልማቱን ማረጋገጥ፡፡

### ራዕይ (Vision)

6. ከ2012-2015 የማዕድን ሀብታችንን የውጪ ምንዛሪ አስተዋፅኦን በ10 እጥፍ ማሳደግና ለኢንዱስትሪው ልማት የጀርባ አጥንት መሆን

### ሥልጣንና ተግባር

7. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት የተለያዩ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡እነዚህም፡-

- የማዕድን ልማቱ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- የማዕድን መረጃዎችን በአግባቡ እንዲሰበሰቡ፣እንዲጠበቁና ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
- ለማዕድን ፍለጋና ልማቱ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የማዕድን ኢንቨስትመንትን ያበረታታል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ህጋዊ መስመር እንዲይዙ ያደርጋል፤

- የማዕድን ልማቱን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማስልጠኛ ተቋሞችን እንደአስፈላጊነቱ ያደራጃል፤
- ስለዘርፉ ልማትና አጠቃቀም ፖሊስና ሕግ ያዘጋጃል፤
- በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች ፈቃድ ይሰጣል፤ በገቡት ውል መሰረትም ስራቸውን ማካሄዳቸውንና የክፍያ ግዴታዎቻቸውን መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፤ የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ሀይል**

8. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው በተቋሙ የበላይ አመራር አካል በሆኑ በሚኒስትር ሲሆን አንድ ሚኒስትር ዴኤታ፣ አስራ ሦስት(13) ዳይሬክቶሬቶች፣ እና አራት (የለዉጥ አመራር ጽ/ቤት፣ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግልጽነት ኢኒሼቲቭ ማስፈጸሚያ ጽ/ቤት፣ የስነ-ምግባር ጽ/ቤት እና የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤት) ጽ/ቤቶች ይገኛሉ (አባሪ 1)፡፡ በሚኒሰቴር መ/ቤቱ በህዳር ወር 2005 ዓ.ም 152 ወንድ እና 115 ሴት ሠራተኞች በድምሩ 276 ጠቅላላ ሰራተኞች ነበሩት፡፡

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ**

9. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት የሚመደብለት በጀት ሲሆን፣ ባለፉት ሦስት ኣመታት የተመደበለት በጀት እና ሥራ ላይ የዋለው በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ዓመተ ምህረት | የገንዘብ ምንጭ | | ጠቅላላ የተገኘ ገንዘብ | ስራ ላይ የዋለ የገንዘብ መጠን | | ጠቅላላ ስራ ላይ የዋለ ገንዘብ | በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከመደበኛ | ከውጪ ብድርና ዕርዳታ | | ከመደበኛ | ከውጪ ብድርና ዕርዳታ | | |
| 2001 | 11,992,183.00 | 18,343,300.00 | 30,335,483.00 | 10,851,514.23 | 6,527,929.00 | 17,379,443.23 | 57% |
| 2002 | 14,792,137.64 | 10,821,145.00 | 25,613,282.64 | 12,331,685.96 | 7,606,568.00 | 19,938,253.96 | 78% |
| 2003 | 15,919,727.58 | 3,082,836.00 | 19,002,563.58 | 15,144,830.98 | 8,093,939.00 | 23,238,769.98 | 122% |
| 2004 | 27.5 ሚሊዮን | 3.3 ሚሊዮን | 30.8 ሚሊዮን | 19.4 ሚሊዮን | 2.1 ሚሊዮን | 21.5 ሚሊዮን | 70% |

**የኦዲቱ ዓላማ**

10. የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ልማት ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት ፣ የሀገርና የመንግስትን ጥቅም በሚያስከብር መንገድ መዘርጋቱን እና ልማቱ የአካባቢንና የህብረተሰቡን ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን በማጣራት በኦዲቱ የሚገኙ

ድክመቶች ካሉ መንስዔዎቻቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫና የመመዘኛ መስፈርት

11. የተለየውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ሦስት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-
    1. የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ በማልማት ስራ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፤
    2. የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎች ለማስወገድና ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፤ እና
    3. የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ የሚሉት ናቸው፡፡

12. የተመረጡትን እነዚህ ሦስት የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ኦዲት ለማድረግ 48 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡ በተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶቹም ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

13. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡ የዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ 2002 እስከ 2004 በጀት ዓመት ያለውን ጊዜ እና የ2005 በጀት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ ያለውን ጊዜ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር ነው፡፡

14. ለኦዲቱ የሚሆኑ መረጃዎች ከማዕድን ሚኒስቴር፣ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልሉ ውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ፣ በጉጂ ዞን የኦዶ ሻኪሶ ወረዳ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የክልሉ የማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ፣ ከሐዋሳ ከተማ፣ ከሀዲያ ዞን ማዕድንና ኢነርጂ መምሪያ፤ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በአካባቢ ባለሥልጣን የማዕድን ሀብት ጥናትና አስተዳደር ሽርሽን፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እንዲሁም በናሙና ከተመረጡ በእነዚህ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ በማዕድን ሚኒስቴርም ሆነ በክልሎች በኩል የማዕድን ማምረት ፈቃድ የተሰጣቸውን ድርጅቶችና ማህበራት መጠይቅ በማቅረብ፣ መረጃዎችን በመከለስና የመስክ ጉብኝት በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል (አባሪ 2)፡፡ ለቀሪዎቹ ክልሎች ደግሞ መጠይቅ ተልኮ፤ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድንና

ኢነርጂ ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ ሌሎቹ ክልሎች ምላሽ አልሰጡም፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process descriptions)

### የማዕድን ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

15. ዳይሬክቱሬቱ የአገሪቱንና የአለም አቀፉን የማዕድን ምርት ፍላጎት በመከተል የኢንቨስትመንት አቅጣጫዎች የማረጋገጥ ልማታዊ ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ ፈቃድ የመስጠት፣ የመከታተልና እገዛ የማድረግ፣ የልማት መረጃዎች የማስተዋወቅ፣ ከማዕድን የሚገኘው ልዩ ልዩ ገቢ የማሰባሰብና የማሳወቅ ሥራዎችን በዋናነት ያከናውናል፡፡

### የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት

16. የተጀመረው ወርቅና ሌሎች ጌጣጌጥ ማዕድናት ለብሔራዊ ባንክና ለውጪ ገበያ የማቅረብ ስራ ቀጣይነት እንዲኖረው ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት በመስራት አምራቾች እንዲደራጁ በማድረግና የቴክኒክና የማምረቻ መሳሪያዎች እንዲያገኙ በመደገፍ ፍትሀዊ የሆነ የገበያ ሥርዓትን የመዘርጋትሥራዎችን በዋናነት ያከናውናል፡፡

### የአካባቢ ማህበረሰብ ልማት ዩኒት

17. ይህ ዳይሬክቶሬት ከፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነዶችን መርምሮ የማረጋገጥ ኃላፊነት በቁጥር መተ14/13 የካቲት 4 ቀን 2003 ዓ.ም ውክልና ተሰጥቶታል፡፡ በማዕድንና ፔትሮሊየም ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በአካባቢና በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ በመከታተልና በመቆጣጠር አካባቢዎች መልሰው እንዲያገግሙና ህብረተሰቡም ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ዋና ዋና ሥራዎችን በዋናነት ያከናውናል(አባሪ 3)፡፡

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### 2.1 የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ በማልማት ስራ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ  የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፤

#### በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓትን በተመለከተ፤

18. በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እና የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ በማዕድን ሥራ ላይ ለመሰማራት ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል ግልጽ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ የማዕድን ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት  የማዕድን ፈቃድ ጠያቂው አስፈላጊዉን የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ብቃት ያለዉ መሆኑ ሊያቀርብና ትክክለኘነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

19. ይሁን እንጂ በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘረጋ ቢሆንም፤ በናሙና ከተመረጡና በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማምረት ፈቃድ ከተሰጣቸው 21 ባለፈቃዶች ውስጥ 14ቱ (67%) የተቀመጠዉን መስፈርት (ለምሳሌ መታወቂያ ካርድ/ ፓስፖርት (ID Card/passport), የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study), የአመልካቹን ፋይናንስ ሁኔታን የሚያሳይ (Evidence verifying the financial status of the applicant), የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሪፖርት (Environmental impact assessment{EIA} report), የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (Tax identification Number {TIN}), የማህበር ህገ ደንብ (Article of association, Memorandum of association, Legal form) አሟልተው ፍቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት መረጃ አልቀረበም(አባሪ 4)፡፡

20. የማዕድን ሚኒስቴር ኃላፊዎች ስለጉዳዩ  ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ፣ ማስረጃዎቹ በተለያየ ቦታ የተቀመጡ በመሆናቸው በተፈጠረ የመረጃ ክፍተት ሊሆን እንደሚችል እንጂ  የተጠቀሱት መስፈርቶች ሳይሟሉ ፈቃድ እንደማይሰጥ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተባሉት ሰነዶች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ስላልቀረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

21. ስለሆነም በማዕድን ሥራ ላይ ለመሰማራት ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል የተዘጋጀው ግልጽ የሆነ መስፈርት ሳያሟሉ ፍቃድ መሰጠቱ የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱ ተአማኒ እንዳይሆን ስለሚያደርገው መረጃዎቹ በአንድ ቦታ ተሟልተው ወይም የተቀመጡበት ቦታ ተጠቅሶ በተፈለጉ ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ ይገባል፡፡

## ለዱር እንስሳት እና ለተፈጥሮ ደን ሀብት ጥበቃ በተከለሉ አካባቢዎች የማዕድን ፈቃድ የማይሰጥ መሆኑን በተመለከተ

22. የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀፅ 6/3መ ለብሔራዊ ፓርክነት በተከለሉ ሥፍራዎች የማዕድን ማምረት ፈቃድ እንደማይሰጥ፣ በዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ድንጋጌ መሰረት በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚካሄደው ማንኛውም የኢንቨስትመንት ተግባር በዱር እንስሳቱንና የመኖርያ አካባቢያቸውን ሕልውና በዘላቂነት የሚያረጋግጥና በዱር እንስሳቱና አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድር መሆን መረጋገጥ እንደሚገባው ይደነግጋል፡፡

23. በመሆኑም የማዕድን ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የማዕድን ልማት ፈቃድ የተጠየቀበት አካባቢ ለዱር እንስሳት ጥበቃ ያልተከለለ እና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሲባል፣ በተለየ ሁኔታ ጥበቃ የማይደረግለት መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ እና የታቀደው የማዕድን ልማት በዱር እንስሳት እና በመኖሪያቸው አካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያሳድር መሆኑና የአካባቢያቸው ህልውና በዘላቂነት የሚጠበቅ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

24. ይሁን እንጂ፣ የአብጃታ ሶዳ አሽ አክስዮን ማህበር በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን አዳሚ ቱሉ ጁዶ ኮምቦልቻ ወረዳ ውስጥ ከአብጃታ ሐይቅ ውስጥ የሶዳ አሽ ማዕድን ለማምረት ፈቃድ ሲጠይቅ፤ የማዕድን ፈቃዱ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተለይም ማዕድኑ የሚገኝበትን ሐይቅ የሚጋራው የአብጃታ-ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክን በባለቤትነት የሚያስተዳደረው የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን አስተያየት ተጠይቆ በቁጥር ደማ1/22/02 ነሐሴ 21 ቀን 2002 ለአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ዩኒት በተፃፈ ደብዳቤ ኢንቨስትመንቱ ቢቀጥልና ይበልጥም ቢስፋፋ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን እና ፈቃዱ መሰጠት እንደሌለበት አስተያየት ያቀረበና፤ በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ *የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ዩኒት በጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ* ተግባራዊነቱ እንዲቀጥል ይሁንታ መሰጠት እንደሌለበት አስተያየት የሰጠ ቢሆን የአብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ ይዞታ ክልልን የጨመረ ከ28,800 ስኬየር ኪሎ ሜትር በሆነ ቦታ ላይ የሶዳ አሽ እንዲያመርት የማዕድን ፈቃድ ለአክስዮን ማህበሩ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

25. በተጨማሪም ለአክስዮን ማህበሩ የተሰጠው ቦታ ይዞታ ሲታይ የአብጃታ ኃይቅን መሉ በሙሉ የጨመረ ሆኖ የተገኘ ሲሆን፣ ነገር ግን ቀደም ብሎ የአብጃታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ ከክልሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የፓርኩ ወሰን ተረጋግጦ የወሰን መለያ ችካል መተከሉን ይህም አብዛኛው የቦታውን ይዞታ ያካለለ ለመሆኑ በኦዲቱ ተመልክተናል፡፡

26. እንደዚሁም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ኢሉ አባቦራ ዞን ያዩ ወረዳ የኮል ፎስፌት ማዳበርያ ኮምፕሌክስ ፕሮጀክት ለብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ሊተገበርበት የታሰበበት ቦታ

ሙሉ በሙሉ በቅርቡ Biosphere Reserve ተብሎ በUNESCO እውቅና ያገኘ የደን ቦታ በመሆኑ፣ የያዩ ጥብቅ የጫካ ቡና (Yayu coffee forest Biosphere Reserve) ከየትኛውም አካባቢ የጫካ ቡና /wild Arabica coffee/ በብዛት በውስጡ የያዘና በብዝኃ-ሕይወት (Biodiversity) የበለፀገ በመሆኑ የደን ቦታውን ከአላማው ውጭ ማዋል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ Biosphere Reserve የተቋቋመበትን ቀጣይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ፈቃዱ ቢሰጥ አካባቢው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያላቸውን ስጋት በቁጥር DHBBBO/BAJ-/27/213 በጥቅምት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ለማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤት የተገለፀና ኮርፖሬሽኑም የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት አስጠንቶ ሳያቀርብ፣ የድንጋይ ከሰል ማዕድን የማምረት ፈቃድ የተሰጠው መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

27. ስለጉዳዩ የማዕድን ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የእቢጃታ ሶዳ አሽ አክስዮን ማህበር ቀደም ሲል ከኦሮሚያ ክልል የማዕድን ፈቃድ አውጥቶ ሲሠራ የነበረ የመንግስት የልማት ድርጅት በመሆኑ፣ ወደ ጋራ ልማት (Joint venture) ሲዞር፣ ፈቃዱ በፌደራል ደረጃ መሰጠት ስለነበረበት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት (EIA) ማቅረብ ሳያስፈልገው የአካባቢ ኦዲት (Environmental Audit) አከናውነው እንዲያቀርቡ ተደርጎ ፈቃዱ መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡ የኮል ፎስፌት ማዳበርያ ኮምፕሌክስ ፕሮጀክትን በተመለከተ ደግሞ፤ ለረጅም ጊዜ በጥናት ላይ የነበረና በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ሥር በሚመራ አካል ፕሮጀክቱ ጠቀሜታው የበለጠ ለመሆኑ ትንታኔ (Cost benefit analysis) ተሰርቶና አዋጭነቱ ተረጋግጦ እንዲሁም የማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 መንግሥት ለብሔራዊ ጥቅም ሲባል የተከለከለ ማንኛውንም ሥፍራ ለማዕድን ሥራ ክፍት እንዲሆን ሊፈቅድ የሚችል በመሆኑ፤ ፍቃድ የተሰጠ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ (Exit conference) ወቅት ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ፈቃድ የተሰጠው ፕሮጀክት ጠቀሜታ የበለጠ ለመሆኑ ትንታኔ (Cost benefit analysis) የተሰራበት ለመሆኑ በፈቃድ ሰጪው አካል መረጃው ባለመያዙ አልቀረበም፡፡

28. ስለሆነም ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የሚመለከታቸው አካላት የሚሰጡት አስተያየት ተግባራዊ ካልተደረገ ወይም ጉዳትና ጥቅሙ (Cost benefit analysis) ተተንትኖ ካልተወሰነ የማዕድን ሀብት የአካባቢንና የህብረተሰቡን ደህንነት በጠበቀ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ ካለመቻሉም በላይ በአንድ ይዞታ ላይ ለተለያየ አካላት ይዞታ ማረጋገጫ ሊሰጥ ስለሚቻል በሚካሄደው ልማት እንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

**የማዕድን ቅኝት፣ የምርመራ እና የማምረት ፈቃዶች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜን በተመለከተ፤**

29. የቅኝት ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለ18 ወራት ብቻ፣ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ደግሞ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለ3 ዓመት ብቻ መሆን እና ከ3 ዓመት በኃላ መቀጠል ለሚፈልግ ለተከታታይ 7 ዓመት በየዓመቱ የስራ ፕሮግራም በማቅረብ የምርመራ ፈቃዱን ማደስ ይኖርበታል፡፡ የማዕድን ምርመራ ፍቃድ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ዉስጥ ባለፈቃዱ የምርመራ ስራዉን መጀመር ይኖርበታል፡፡ የማዕድን የማምረት ባለፍቃድ ፍቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ዉስጥ የምርት ሥራዉን መጀመር አለበት፡፡

30. ይሁን እንጂ ንዮታ ሚንራልስ ኢትዮጵያ (NYOTA Minerals Ethiopia LTD) በኦሮሚያ ክልል በተለምዶ ስሙ ዩብዶ በተባለበት ቦታ የምርመራ ፈቃድ እ.ኤ.አ. ከ6/29/2004 እስከ 6/28/2011 እ.አ.አ ለ4ተኛ ጊዜ ያደሰ ቢሆንም፣ እ.ኤ.አ. ከ6/28/2011 በኃላ የታደሰ ወይም የተሰረዘ ስለመሆኑ፣ ሚድሮክ ጎልድ ፒ.ኤል.ሲ. (Midroc Gold Mine PLC) በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ባሩዳ-ቡለን፣ አበላሩስ በተባለበት ቦታ የወሰደውን የማዕድን ምርመራ ፈቃድ እ.ኤ.አ. በ3/22/2005 እስከ 3/21/2012 ለ4ኛ ጊዜ ያደሰ መሆኑን በመረጃ ቋቱ ላይ የሚታይ ቢሆንም፣ ከዚያ በኃላ ለማደሱ መረጃዎች ከባለ ፍቃዱ ፋይል ውስጥ ለማግኘት ያልተቻለ መሆኑን፣ እንዲሁም የለገ ደንቢ የምርመራ ፍቃድ እ.ኤ.አ. ከ3/29/1998 እስከ 3/28/2001 ድረስ የወሰደ ቢሆንም፣ እ.ኤ.አ. ከ2001 በኃላ የታደሰ ወይም የተሰረዘ ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡

31. ብሔራዊ የማዕድን ኮርፖሬሽን (National Mining Corporation) በትግራይ ክልል ጪኒ እና ወርቅ አምባ (Chini & wok Amba) አካባቢ እ.ኤ.አ. ከ2007/08 ጀምሮ የወሰደው የወርቅ ፍለጋ ፈቃድ ፈቃዱ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ የታደሰ ወይም የተሰረዘ ስለመሆኑ፣ አዲስ ሪሶርስስ ዲቨሎፕመንት ፒ.ኤል.ሲ. (Addis Resources Development PLC) በቤንሻጉል ጉሙዝ ክልል በአሶሳ ዞን አሶሳ ወረዳ አጉሻ በሚባል ቦታ ላይ የምርመራ ፈቃድ እ.ኤ.አ. ከ16/2/2003 እስከ 15/2/2013 ለ6ኛ ጊዜ ያደሰ መሆኑን በመረጃ ቋቱ ላይ የሚታይ ቢሆንም ከ6ኛው ዕድሳት በፊት ላሉት ዕድሳቶች የስራ ፕሮግራም ያቀረቡ ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡

32. በአጠቃላይ እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ መታደስ ወይም መሰረዝ የነበረባቸው 81 የምርመራ ፈቃዶች ለመታደሳቸው፣ እንዲያሳድሱ ማሳሰቢያ የተሰጠበት ወይም ፈቃዳቸው ለመሰረዙ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም (አባሪ 5)፡፡

33. ስለጉዳዩ የማዕድን ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኒዮታ ሚንራል ኢትዮጵያ ሊምትድ ባከናወኑት የምርመራ ሥራ ሊመረት የሚችል አዋጭ የሆነ የወርቅ ክምችት ያገኙ በመሆኑ የምርት ፈቃድ ጥያቄ አቅርበው በድርድር ላይ እንደሚገኙ፣ የመተከል

የወርቅ ምርመራ ፈቃድ የታደሰ መሆኑን፣ የለገደንቢ ምርመራ ፈቃድ በአካባቢው በተከሰተው ችግር ምክንያት ሳይታደስ እንዲቆይ የተደረገ መሆኑንና ችግሩን ለመፍታት ከክልሉ ጋር በመቀናጀት ጥረት እያደረጉ መሆኑን፣ ብሔራዊ የማዕድን ኮርፖሬሽን ለረዥም ዓመታት ባከናወኑት የምርመራ ሥራ የሰበሰቡትን መረጃ በአማካሪ ድርጅት በማስገምገም የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት ሪፖርት አቅርበው አበረታች የወርቅ ክምችት የተገኘ መሆኑ በመታወቁ ቀሪ ሥራዎችን በአጭር ጊዜ አጠናቅቀው ወደ ምርት እንዲገቡ አቅጣጫ ተቀምጦ እየሠሩ እንደሚገኙ፣ የአዲስ ሪሶርስ ዲቨሎፕመንት ፒ.ኤል.ሲ. ፈቃድ በክልል የተሰጠና ሲተዳደር የቆየ የነበረና በማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሠረት ወደ ማዕድን ሚኒስቴር የመጣ እንደሆነ ገልጸው፣ በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት መ/ቤቱ ባለው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት ሳይታደሱ የቆዩ፣ መሠረዝ ያለባቸው ፈቃዶች እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የአስተዳደር ሥራዎችን ለማጥራት ፈቃድ መስጠት አቁመው በመሥራት ላይ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

34. በአዋጁ ላይ በተቀመጠው መሰረት መታደስ ወይም መሰረዝ ያለባቸው ፈቃዶች ወቅታቸውን ጠብቀው መታደስ ወይም መሰረዝ ካልቻሉ ሀገሪቷ ከልማቱ የምታገኘውን ጥቅም ከማጣቷም በተጨማሪ ሌሎች አካላት ቦታውን ለሌላ ልማት እንዳያውሉ አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**<u>ማዕድን ለማልማት ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በገቡት ውል መሰረት መስራታቸውን በተመለከተ፤</u>**

35. ማዕድን ለማልማት ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በገቡት ውል መሰረት ስራቸውን ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

36. ይሁን እንጂ ድልቢ ኮል ማይኒግ አክስዮን ማህበር በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ዴዶ ወረዳ ውስጥ የድንጋይ ከሰል ለማምረት የማዕድን ማምረት ፈቃድ ሲወስድ በግንቦት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. ዉል ከገባው ግዴታዎች ውስጥ፣ አስራ ሁለት የተለያዩ መሰረተ ልማት ሥራዎች (ለምሳሌ የሁለት ብሎክ ጤና ጣቢያ ግንባታ፣ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የእንስሳት ጤና ኬላ ከነባለሙያ መኖሪያ፣ የውሃ ግንባታ የእጅ ፓምፕ ውሃ ጉድጓድ ብዛት 4 እና ሌሎችም) ከዚህም በተጨማሪ የድርጅቱ ጽ/ቤትና የሰራተኞች መኖርያ የተሰራበት ቦታ ቀደም ሲል የድልቢ ቀበሌ ጤና ኬላ እና የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከል (FTC) ግንባታ የተጀመረበት እንደነበርና ግንባታው የተቋረጠና በድርጅቱ በኩል በቀበሌው ማዕከል እንዲሰራ ስምምነት የነበረ ቢሆንም፣ እስካሁን ከአራት ዓመታት በኃላ ተግባራዊ አለመሆኑ፤ እንዲሁም የማዕድን መሬት ኪራይ የማይከፍል መሆኑ ታውቋል፡፡

37. ችግሩን ለመፍታት የዴዶ ወረዳ አስተዳደር እና የደልቢ ኮል ማዕድን ማምረቻ አክስዮን ማህበር የቦርድ አባላት በጋራ በመሆን አክስዮን ማህበሩ ስለሚያከናውናቸው ሥራዎች የመሰረተ ልማት ስራው እንዲጀመር ኮሚቴ ተቋቁሞ የባንክ ሒሣብ በመክፈት ለአክስዮን ማህበሩ እንዲያሳውቅ እና አክስዮን ማህበሩ ሁለት ሚሊዮን ብር በዝግ ሒሳብ ገቢ እንደሚያደርግ ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ስምምነት ላይ ተደርሶ የነበረ ቢሆንም እስካሁን ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

38. ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ከ4 ዓመታት በላይ መልስ ሳያገኙ የቆዩ እና ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በቁጥር ቋከኑ/አር12/90 ግንቦት 08 ቀን 2004 ዓ.ም የማዕድን ሚኒስቴር አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች እንዲወስድ በተፃፈ ደብዳቤ የተገለፀ ቢሆንም፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ እርምጃ አለመውሰዱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

39. ስለጉዳዩ የማዕድን ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ፈቃዱ የተሰጠው የማዕድን ሚኒስቴር ውክልና ከመሰጠቱ በፊት በፌደራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እንደሆነና ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ ጊዜያት የመስክ ክትትል ሥራ እና ከኩባንያው ጋር ውይይት መካሄዱን፣ በተጨማሪም ኩባንያው በገጠመው የገበያ ችግር ምክንያት ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ያጋጠመው እንደሆነና ኩባንያው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ያሳወቀ መሆኑ፣ ይህንኑ ችግር በመቅረፍ ሌሎች ግዴታዎቹን ኩባንያው እንዲወጣ ለማስቻል ከሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ድጋፍ እንዲደረግላቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ስለተሰሩ ሥራዎችም ሆኑ ስለተወሰዱ እርምጃዎች የሚያሳይ መረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

40. የማዕድን ባለፈቃዶች ለማህበረሰብ ልማት በገቡት ውል መሰረት የአካባቢውን ህበረተሰብ የሚረዳ የልማት እንቅስቃሴ አለማከናወናቸው የአካባቢው ማህበረሰብ ከልማቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ በልማት እንቅስቃሴውም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲፈጠር በር ይከፍታል፡፡

## <u>የሮያሊቲ፣ እና የመንግስት ነፃ የአክሲዮን ድርሻ ክፍያዎችን በተመለከተ፤</u>

41. የማዕድን ባለፍቃድ ከማምረቻ ቦታ ላይ ከሚያመርተዉ የማዕድን/ናት ምርት በየግዜዉ የሮያሊቲ የቫት፣ የመሬት ኪራይ እና የመንግስት ነፃ የአክሲዎን ድርሻ ክፍያዎችን የሚፈፀምበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና የተዘረጋዉ ስርዓት ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ የመንግስት ነፃ የአክሲዎን ድርሻ በቀድሞው አዋጅ 2% በአዲሱ አዋጅ ደግሞ 5% እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት የመንግስት ነፃ አክስዮን ድርሻ

የሚያስገኘውን ጥቅም በተመለከተ በማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ በናሙና ከተመረጡ 21 ማዕድን አምራቾች ውስጥ 20 ባለፈቃዶች ክፍያ የማይፈፅሙ መሆናቸዉ የሚድሮክ የወርቅ ማዕድን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የትርፍ ድርሻ ክፍፍል በሚያከናውንበት ወቅት ሁሉጊዜ የመንግስት አክስዮን ድርሻን ክፍያ እንደሚፈጽም ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በናሙና ጉብኝት በተደረገባቸው የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የመንግስት ነፃ የአክስዮን ድርሻ እየተሰበሰበ አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

43. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የመንግስት ነፃ የአክስዮን ድርሻ (Free equity) የሚሠበሰበው ከግብር በኋላ ከሚገኝ ትርፍ ላይ እንደሆነ፣ ብዙዎቹ የምርት ባለፍቃዶች ምርት የጀመሩት በቅርብ ጊዜ በመሆኑ፣ የቅድመ ምርት እና የቋሚ ዕቃዎች ወጪዎችን በማዕድን ህጉ መሠረት መልሰው ማትረፍ መጀመራቸውን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ፣ ሆኖም ይህንን በባለቤትነት የሚከታተለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡ የመንግስት ነፃ የአክስዮን ድርሻን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከየካቲት 2002 ዓ.ም በኃላ ከሚድሮክ ወርቅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሚሰበሰበው የመንግስት የነፃ አክስዮን ድርሻ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል እንዲሰበሰብ ውክልና የተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የሰጣቸው አካላት በገቡት ውል እና በማዕድን አዋጅ መሰረት የመንግስት ነጻ የአክስዮን ድርሻ በየጊዜው ለመክፈላቸው እና የማምረት ፈቃድ የወሰዱ ድርጅቶች በኪሳራ እየተንቀሳቀሱ ለመሆኑ የራሱን ማጣራት ባለማድረጉ የተሰጠውን መላሽ አልተቀበልነውም፡፡

44. ሮያሊቲን በተመለከተ ደግሞ የሶዳ አሽ ለማምረት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የማምረት ፈቃድ የወሰደው የአብጂያታ ሶዳ አሽ አክስዮን ማህበር ሮያሊቲን በተመለከተ ፈቃድ ከማውጣታቸው በፊት ለገቢዎችና ጉሙሩክ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር እስከ መስከረም 2004 ዓ.ም ድረስ ክፍያ የከፈሉ መሆኑ ፈቃድ ከወሰዱ ከመስከረም 2004 ዓ.ም. በኃላ ግን ክፍያ እንዳልፈፀሙ ታውቋል፡፡ አክስዮን ማህበሩ የማዕድን ፈቃድ የወጣው በአቢጂያታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር ስም ሲሆን ከመንግስት ጋር ብሔራዊ የማዕድን ኮርፖሬሽን ጆይንት ቬንቸር ውል መሰረት ግን ሁሉም ሰነዶች ያሉት በአቢጃታ ሻላ ሶዳ አሽ አክስዮን ማህበር ስም በመሆኑና በዚህም ምክንያት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሮያሊቲ ክፍያውን ለመፈፀም ቼክ ሲልኩ፣ ድርጅቱ በዚህ ስም ፈቃድ አልወሰደም በማለት ክፍያውን ላለፉት 3 የሩብ ዓመት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳልተቀበለና ችግሩን ለመፍታት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

45. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ፈቃዱ ባልተሠጠበት ስም ገቢ ማድረግ እንደማይቻል፣ ሆኖም ባለፈቃዱ ፈቃዱን እንዲያስተላልፍ እንደተነገረውና

ቢዘገይም በአሁኑ ወቅት ጥያቄ ቀርቦ በሂደት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተጠቀሰው ምላሽ ቢሰጥም፣ የፈቃድ ዝውውር እንዲያደርጉ ለአክስዮን ማህበሩ የተገለጸበት መረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

46. በክልሎች በባህላዊ መንገድ ከሚመረት ወርቅ ሮያሊቲን ለመሰብሰብ የሚያስችል ህግ በክልሎች በኩል ወጥቶ ተግባራዊ ያልተደረገ እና ሮያሊቲም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል እና ኦሮሚያ ክልል የማይሰበስቡ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ገልጸዋል፡፡

47. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በባህላዊ መንገድ ለማምረት ፈቃድ የወሰዱ የወርቅ አምራቾች(የሕ/ሥ/ማህበራት) ላመረቱት ምርት ሮያሊቲ እንዲከፍሉ ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም፣ ክልሎች ከአምራቾች ሳይሆን ከአዘዋዋሪዎች ለመሰበሰብ በመሞከራቸው የተፈጠረ ክፍተት መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልፀዋል፡፡

48. በአዋጅ በተደነገገው መሰረት የመንግስት ነፃ የአክሲዮን ድርሻ በፌደራልም ሆነ በክልሎች በኩል በተጠናከረ መልክ አለመሰብሰቡ ሀገሪቱ ከማዕድን ዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ገቢ እንዳታገኝ ያደርጋታል፡፡

**<u>የማዕድን ፍቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች የአፈፃፀም ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ፤</u>**

49. ማንኛውም ባለፈቃድ የአፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርብና በሪፖርቱ መሰረት የታዩ ክፍተቶች/ችግሮች ላይ አስፈላጊው የእርምት እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

50. ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡ 21 ባለፈቃዶች ውስጥ 20ዎቹ ወቅቱን ጠብቀው ሪፖርት የማያቀርቡ መሆናቸው እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በአካል በመገኘት ክትትል የማይደረግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ እንዲሁም በናሙና ከታዩት ከ2003 እስከ 2004 የ20 ባለፈቃድ የቀረቡ የሩብ ዓመት የአፈጻጸም ሪፖርቶች ላይ የሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች/ችግሮች ተለይተው የሚኒስቴር መ/ቤቱ አስፈላጊው የእርምት እርምጃ ወይም ምላሽ እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

51. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በአሁኑ ወቅት ባለው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት በመስክ እና በቢሮ ክትትል እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የአስተዳደር ሥራዎችን ለማጥራት ፈቃድ አቁመን በመሥራት ላይ እንደሚገኙ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

52. የማዕድን ባለፈቃዶች ወቅቱን ጠብቀው በየሩብ ዓመቱ ለፍቃድ ሰጪው አካል የአፈፃፀም ሪፖርት አለማቅረባቸው እንዲሁም በሚቀረቡት የአፈጻጸም ችግሮች ላይ ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰዱ ባለፈቃዶች በገቡት ውል መሰረት እየሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳይቻል

ከማድረጉም በላይ በማዕድን ልማቱ ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች በፈቃድ ሰጪው አካል አፋጣኝ ምላሽ/መፍትሄ አለመሰጠቱ በልማት ሥራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

**<u>በማዕድን ልማት ለሚሳተፉ አካላት ለልማቱ የሚያግዙ መሳሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከቀረጥ ነፃ የማስገባት መብትን በተመለከተ፤</u>**

53. በማዕድን ልማት ለሚሳተፉ አካላት ለልማቱ የሚያግዙ መሳሪያዎች ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና የገቡት መሳሪያዎች በትክክል ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

54. በማዕድን ልማት ለሚሳተፉ አካላት ለልማቱ የሚያግዙ መሳሪያዎች ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ የማዕድን ሚኒስቴር ከቀረጥ ነፃ የገቡት መሳሪያዎች በትክክል ስራ ላይ መሆናቸዉን በሪፖርት መልክ ክትትል ከማድረግ ውጪ በአካል በመገኘት ክትትል የማይደረግ እና ለተባለለት የልማት ሥራ ብቻ እየዋለ ለመሆኑ የማይረጋገጥ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

55. በቀረጥና ታክስ ዙሪያ የሚድሮክ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ከመንግስት ወደ ግል ይዞታነት እ.ኤ.አ. በ1997 ዓ.ም. ሲዛወር የማዕድን ፍለጋ እና ማምረት ለ20 ዓመታት ፀንቶ የሚቆይ ስምምነት (Agreement) መፈራረሙ፣ በተመሳሳይ መልኩ የሳካሮ የከርሰ ምድር ማዕድን ልማትና ማምረት ለ20 ዓመታት ፀንቶ የሚቆይ ስምምነት እ.ኤ.አ በ2009 ዓ.ም. የተፈራረሙ እንደሆነና፤ በእነዚህ ሁለት ስምምነቶች መሰረት ኩባንያው ለማምረት ተግባሩ የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች፤ ቋሚ ዕቃዎችና መለዋወጫዎች (የቤት አውቶሞቢልንና መለዋወጫዎቻቸውን ሳይጨምር) ከማንኛውም የጉምሩክ ታክስና ቀረጥ ነፃ አድርጎ ማስገባት እንደሚችል በግልፅ ሰፍሮ የሚገኝ ቢሆንም በ2002 ዓ.ም. በወጣው አዋጅን ምክንያት በማድረግ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እንዳያስገቡ መከልከላቸውን ገልጸዋል፡፡

56. በአሁን ወቅት ለልማትም ሆነ ለማምረት የሚያስፈልጉዋቸውን ዕቃዎች በሙሉ የጉምሩክ ታክስና ቀረጥ እንዲከፍሉ በመገደዳቸው የማምረት ተግባሩን ላለማቋረጥ ሲባል ብቻ የተጠየቁትን ቀረጥና ታክስ እየከፈሉ መሆኑን በአሁን ወቅት እ.ኤ.አ እስከ መስከረም 2012 ድረስ ብር 236,508,239.00 (ሁለት መቶ ሠላሳ ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር) በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ምክንያት የተያዘባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል ችግራቸውን አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀጽ 81 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በውይይት እንዲፈታ ጥያቄ ያቀረቡ እና እስከ አሁን ምላሽ አለማግኘታቸውን አስታውቀዋል፡፡ አቤቱታቸው ምላሽ አለማግኘቱ ፈታኝ የሆነ የሚያስቸግር አሰራር ላይ

እንደጣላቸው በዚህ መልክ መቀጠል እንደማይችሉ ሆኖም ውሳኔን በመጠበቅ መታገስን የመረጡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

57. ስለጉዳዩ በማዕድን ሚኒስቴር የማዕድን ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተወካይ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የሚድሮክ ወርቅ ማዕድንን በተመለከተም አዲሱ አዋጅ ከቀረጥ ነጻ የሚፈቀድበትን ጊዜ በመገደቡ የጊዜው ገደብ ካለፈ በኃላ መፍቀድ እንደማይቻል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንም እንደማይቀበላቸው ገልጸዋል፡፡ ስለአጠቃላይ ጉዳዩ ደግሞ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎቹ በአሁኑ ወቅት መ/ቤቱ ባለው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት በመስክ እና በቢሮ ክትትል እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የአስተዳደር ሥራዎችን ለማጥራት ፈቃድ አቁመን በመሥራት ላይ እንደሚገኙ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

58. ለማዕድን ስራ ከቀረጥ ነፃ የገቡት መሳሪያዎች በትክክል ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትል የማይደረግ ከሆነ ከዓላማ ውጪ ለሌላ ተግባር እንዲያውሉት በር የሚከፍት ሲሆን የሚያጋጥሙ ከቀረጥ ነፃ ጋር የተያያዙ ችግሮችንም በአዋጁ መሰረት በውይይት በፍጥነት አለመፍታት በማዕድን ልማቱና ወደ ልማቱ ለመምጣት የሚያስቡ ባለሀብቶች ላይ አሉታዊ ሁኔታ ሊያሳድር ይችላል፡፡

## 2.2 የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎች ለማስወገድና ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፤

### የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያን በተመለከተ፤

59. የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግና የተዘጋጀውም መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት ሊሰራጭ እና አፈጻጸሙም ላይ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

60. ይሁን እንጂ የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ መዘጋጀት እንዳለበት በማዕድን ፖሊሲ ላይ የሚያዝ ቢሆንም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተዘጋጀ እና ለሚመለከታቸው አካላት ያልተሰራጨ መሆኑን በኦዲቱ ታውቋል፡፡

61. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በአሁኑ ወቅት የማዕድን አዋጅን መሰረት በማድረግ ደንብ እና መመሪያዎችን እያዘጋጁ እንደሚገኙ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

62. የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወጥ የሆነ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት መሰራጨት ባለመቻሉ በዘርፉ የልማት ስራዎች ምክንያት በአካባቢ ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተፅዕኖዎች በአግባቡ መተዳደራቸውን ለመቆጣጠር አይቻልም፡፡

### የማዕድን ፈቃድ ጠያቂዎች ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ማቅረብን በተመለከተ፤

63. የማዕድን ፈቃድ ጠያቂዎች ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሊያቀርቡ፣ በፈቃድ ጠያቂዎች የሚቀርቡ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶች ትክክለኛነት ፈቃድ በሚሰጠው አካል የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና የጥናቱ ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

64. ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡ የማምረት ፈቃድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከወሰዱ 21 ባለፈቃዶች ውስጥ 16 ባለፈቃዶች (76%) የሚሆኑት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አቅርበው ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት መረጃው አልቀረበም (አባሪ 5)፡፡

65. የማዕድን ሚኒስቴር ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው ላይ በሰጡት ምላሽ፣ ማስረጃዎቹ በተለያየ ቦታ የተቀመጡ በመሆናቸው በተፈጠረ የመረጃ ክፍተት ሊሆን እንደሚችል እንጂ

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሳይሟላ ፈቃድ እንደማይሰጥ ቢገልጹም የተባሉት መረጃዎች ለኦዲቱ ባለመቅረባቸው የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

66. የዘርፉ አልሚዎች የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አካሂደው ፕሮጀክቶች እንዲተገበሩ ይሁንታ ካልተሰጣቸው በልማቱ ምክንያት በአካባቢና በማህበረሰቡ ላይ የሚደርሰውን ችግር ለማወቅ ካለመቻሉም በተጨማሪ በልማቱ ምክንያት ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ ማበጀት አይቻልም፡፡

## ህብረተሰቡ ከማዕድን ልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓትን በተመለከተ፤

67. ህብረተሰቡ ከማዕድን ልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊነቱ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ከአካባቢ ማህበረሰቦች፣ ከማዕድን ስራ ከተሰማሩ ባለሀብቶችና ከክልል መንግስታት ጋር በመተባበር የተቀናጀ የአካባቢ ልማት እቅድ ሊዘጋጅና ለዚህም የሚያስፈልግ ወጪ/ፈንድ የሚመደብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

68. ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ ከተሰጣቸው ከ21 ውስጥ 20 ባለፈቃዶች በአካባቢ ልማት ላይ ብዙ ትኩረት ያለማድረጋቸው፣ ባለፈቃዶቹ ከአካባቢው መስተዳድርና ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የተቀናጀ የአካባቢ ልማት ዕቅድ የማይዘጋጅ መሆኑን፣ የአካባቢ ልማት እቅድ እንዲዘጋጅ የሚያደርግ ስርዓት ተዘርገቶ ተግባራዊ አለመደረጉ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

69. ከዚህ በተጨማሪም የሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ የድሮው አዋጅ የአካባቢ ልማት እቅድን በተመለከተ የሚለው ነገር ያለመኖሩ በ678/2002 የማዕድን አዋጅ ግን የሚያዝ መሆኑን በመረዳት በየዓመቱ ገንዘብ እንደሚመድቡ ነገር ግን ለማን ማስገባት እንዳለባቸው ባለማወቃቸው ለማዕድን ሚኒስቴር ደብዳቤ ቢፅፉም ምላሽ እስካሁን ያላገኙ መሆኑን፣ አቢጂያታ ሶዳ አክሲዮን ማህበር በየዓመቱ ለትምህርት፣ ለጤና እና ለውኃ የሚውል ገንዘብ ውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት የሚያስቀምጡ መሆኑንና ገንዘቡን ግን ለማን ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው ያሳወቃቸው አካል ባለመኖሩ ምክንያት በገንዘቡ የአካበቢው ህብረተሰብ ተጠቃሚ ሊሆን አለመቻሉ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

70. ነገር ግን አንዳንድ የማዕድን ልማት ባለፈቃዶች ከራስ ተነሳሽነትና አስገዳጅ ሁኔታ በሌለበት ሁኔታ የማዕድን ስራ በሚሰሩበት አካባቢ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመሆን የሚሰሩ ስራዎች መኖራቸውን በኦዲቱ ለመመልከት ችለናል፡፡ ቀሪዎቹ ባለፈቃዶች ፈቃድ ሲሰጣቸው በውሉ ላይ ከሚገለጽ ለዚህ ተግባር እንመድባለን ብለው ከሚገልጹት የገንዘብ መጠን በስተቀር ፈንዱን ስለመመደባቸውም ሆነ የሚመደበው ገንዘብ የት መቀመጥ

እንዳለበትና ስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

71. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፣ ይሄንን ጉዳይ አስመልክቶ እየተዘጋጀ ባለው ደንብ በግልጽ ምላሽ ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን ከአዲሱ የማዕድን አዋጅ በፊት በተለይም የማህበረሰብ ልማት ፈንድ መመደብ አስገዳጅ ሳይሆን በፈቃደኝነት ሲከናወን እንደነበር፣ በአሁኑ ወቅት የሚሰጡ ፈቃዶች የማህበረሰብ ልማት ፈንድ መመደብ ግዴታ እንደሆነና የተመደበው ገንዘብ ሥራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግ መሆኑን፣ ሆኖም ገንዘቡ አንድ የልማት ፕሮጀክት ለማከናወን በቂ እስኪሆን መጠራቀም እንዳለበት፤ የአቢጂያታ ሶዳ አክሲዮን ማህበር ፕሮጀክት ከሚተገበርባቸው የወረዳ አስተዳደሮች ጋር በመሆን የማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን እንዲያቀርቡ እና የተመደበውን ፈንድ ለኩባንያዎቹ የሚያስቀምጡበትን አካውንት በደብዳቤ የተላከላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የተባለው እንቅስቃሴ ስለመከናወኑ መረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

72. ከአካባቢ ማህበረሰቦች፣ ከማዕድን ስራ ከተሰማሩ ባለሀብቶችና ከክልል መንግስታት ጋር በመተባበር የተቀናጀ የአካባቢ ልማት እቅድ እንዲዘጋጅ አለመደረጉና ለዚህም የሚያስፈልግ ወጪ/ፈንድ የሚመደብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ የአካባቢው ማህበረሰብ ከልማቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

## የአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ መመደቡን በተመለከተ፤

73. የአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያ የማዕድን ባለፍቃዶች ፈንድ ሊመድቡና ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚመደበዉ ፈንድ ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

74. ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር እና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ከወሰዱት ባለፈቃዶች ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ፈንድ ፈቃድ ሲሰጣቸው በውሉ ላይ ከሚገለጽ የገንዘብ መጠን በስተቀር የተመደበው ገንዘብ የት መቀመጥ እንዳለበትና ስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

75. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ዴዶ ወረዳ፣ ከደልቢ ኮል ማይኒግ ኃ/የተ/የግል ማህበር የሚጣል ቁልል አፈር (Waste) አያያዝ ላያ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ እንደሚገኝ፣ የድንጋይ ከሰሉ ቁፋሮ እየተደረገ ያለዉ ቦታ መከታ ስላልተሰራለት በከፍተኛ ሁኔታ በጉድጓድና ለሌላ የአካባቢ ናዳ ምክንያት በመሆን ላይ የሚገኝና ምንም የመልሶ ማቋቋም ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤ ከቁፋሮ ቦታ ላይ እየወጣ የሚጣል አፈር የህብረተሰቡን የመጠጥ ዉኃ ጉድጓድ

መዝጋቱ፣ በድርጅቱ የተከመረ አፈር ተንዶ በሸለቆዉ አከባቢ ባሉት ህብረተሰብና ዕፅዋት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማስከተሉ፤ በውል ስምምነቱ መሰረት በማምረት ምክንያት የሚከሰቱ ማንኛውም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ኩባንያው የመከላከል ስራዎች በተከታታይ እንደማያከናውንና ሪፖርት እንደማያቀርብ፣ ውል ቢገባም በውሉ መሰረት የአካባቢ አያያዝ ሪፖርት የማያቀርብ መሆኑን በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን የዴዶ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ለማዕድን ሚኒስቴር በቁጥር A-1/235/03 በነሀሴ 13 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የተገለፀ ቢሆንም፤ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የወሰደው እርምጃ ስለመኖሩ መረጃ አልቀረበም፡፡

76. ለመንገዶች ግንባታና ጥገና አገልግሎት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና በክልል የገጠር መንገድ ባለሥልጣኖች እንዲሁም በእነርሱ በኩል ጨረታ አሸንፈው ኮንትራት የሚወስዱ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በህግ በተደነገገው መሰረት በነፃ የሚጠቀሙ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በማዕድን አዋጁ መሰረት አካባቢን መልሶ ለማቋቋም የሚያገለግል ፈንድ የማይመድቡ እና የመንገድ ግንባታቸውን ጨርሰው ቦታውን ለቀው ከመሄዳቸው በፊት የመልሶ ማቋቋም ስራዎች የማይሰሩ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

77. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ይሄንን ጉዳይ አስመልክቶ እየተዘጋጀ ባለው ደንብ በግልጽ ምላሽ ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን፣ ለዚሁ አፈጻጸም የሚረዳ ደንብና መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡ ከክልል የማዕድን ቢሮዎች፣ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ከክልል የገጠር መንገድ ባለሥልጣኖች ጋር የውይይት መድረክ በመፍጥር የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጡ እንደሚበጅ ገልፀዋል፡፡

78. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና ለመልሶ ማቋቋሚያ የማዕድን ባለፍቃዶች ፈንድ በውሉ ላይ ከማስቀመጥ የዘለለ ፈንዱ የሚቀመጥበት እና በተግባር እንዲውል የሚደረግበት ስርዓት ያለመኖሩ የተመደበው ፈንድ በተግባር ከመዋል ይልቅ በወረቀት ደረጃ እንዲቀር ከማድረጉም በላይ የተተዉ የማዕድን ጉድጓዶች የአካባቢው ህብረተሰብ እና እንስሳትን ለጉዳት ይዳርጋል፡፡

**<u>ለማዕድን ስራ ጤንነትና ደህንነት ደንብና መመሪያን በተመለከተ፤</u>**

79. ለማዕድን ስራ ጤንነትና ደህንነት ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ሊሰራጭ፣ ተግባራዊ ሊደረግ እና የተዘጋጀዉ ደንብና መመሪያ ተግባራዊነት ሊገመገም እና ተግባራዊ በማያደርጉ ላይ ህጋዊ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

80. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ሥራ ጤንነትና ደህንነት መመሪያ ተዘጋጅቶ ለክልል ማዕድን ቢሮዎችም ሆነ የማዕድን ፈቃድ ለተሰጣቸው አካላት የተሰራጨ ለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡

81. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፣ እየተዘጋጀ ባለው ረቂቅ የማዕድን ደንብ ውስጥ የሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት የተካተተ መሆኑን፣ በተጨማሪም የማዕድን የሥራ ላይ ጤንነትና ደህንነት ረቂቅ አዋጅ እራሱን ችሎ እየተዘጋጀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

82. ለማዕድን ስራ ጤንነትና ደህንነት ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት መሰራጨት ባለመቻሉ በማዕድን ልማት ላይ የተሰማሩ አካላት በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዳይሰሩ ከማድረጉም በላይ በመስኩ የተሰማሩ ሠራተኞችን ጤንነት እና ደህንነት በጠበቀ ሁኔታ ልማቱ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡

**<u>የሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ልማት ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ  አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤</u>**

83. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ልማት ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ስርዓት ሊዘረጋና ይህ ሥርዓትም በማዕድን ልማት ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን በአፋጣኝ ለመፍታት እና ለሚነሱ ጥያቄያቸው ተገቢው መልስ በወቅቱ የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

84. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለማዕድን የሚያገለግሉ ቦታዎችን ከክልሎች ጋር በመሆን የካዳስተር ሥርዓት በመዘርጋት ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ዕቃዎችን ባለፈቃዶች ሲጠይቁ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የድጋፍ ደብዳቤ እንደሚጽፍም ታውቋል፡፡ ነገር ግን የሚድሮክ ወርቅ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር የሳካሮን የማዕድን ማምረት ፍቃድ ሲያወጡ በካዳስተሩ መሰረት ድንበራቸው እንዲከለልላቸው ለወረዳው፣ ለዞን እና ለክልሉ አሳውቀው መፍትሄ ስላላገኙ ለማዕድን ሚኒስቴር ቢያሳውቁም እስካሁን ድረስ ይዞታቸው እንዳልተከለለ፤ ፈቃድ የተሰጠበት ቦታ ክልል ውስጥ በአንደኛው ሳይት ላይ ሥራ ከተጀመረ በኃላ በአካባቢው ነዋሪዎች በተተከለው ቡና ተክል ምክንያት ለቁፋሮ የሚሆን ማሽን በቦታው ላይ ተክለው መስራት ያለመቻላቸው፣ በለገደምቢ ወርቅ የማምረት ፍቃድ ክልል ውስጥ በሚገኝ የፈንጂ ማከማቻ መጋዘን አካባቢ ከ 500 ሜትር ባነሰ ርቀት የሰፈሩ ነዋሪዎች ማህበሩ ፈቃድ ሲወስድ የነበሩ ሲሆን፣ እነዚህ የነበሩት የመጀመሪያ ነዋሪዎች ካሳ ተከፍሏቸው የተነሱ ቢሆንም፣ እነሱ ከተነሱ በኃላ ሌሎች መጥተው የሰፈሩ መሆናቸውን እና ነዋሪዎቹ ከሥፍራው እንዲነሱ ጉዳዩን ለወረዳው፣ ለዞኑ፣ ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እንዲሁም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አሳውቀው እልባት አለማግኘታቸው በኦዲቱ ወቅት ገልፀዋል፡፡

85. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ፣ ከማዕድን ሚኒስቴር፣ ከኦሮሚያ ክልል፣ ከዞን፣ ከወረዳ እና ከሚድሮክ የተውጣጣ ኮሚቴ ተዋቅሮ ጉዳዩ እየተጠና መሆኑን ገልጸዋል፡፡

86. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና በክልል የገጠር መንገድ ባለሥልጣኖች ለመንገድ ግንባታና ጥገና በህግ በተደነገገው መሰረት በነፃ የኮንስትራክሽን ማዕድናት የሚጠቀሙ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የኮንስትራክሽን ማዕድን ቦታውን ሲወስዱ፤ የሚኒስቴር መ/ቤቱንም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች/ ኤጀንሲዎች እንዲያውቁ የማይደረግ መሆኑን፣ የኮንስትራክሽን ማዕድኑን ከመቼ እስከ መቼ እንደሚጠቀሙ በግልጽ ያልተቀመጠ እና ሥራው ሲጠናቀቅ የማምረቻ ሥፍራውን የማይመልሱ መኖራቸው፣ የኮንስትራክሽን ማዕድኑን ከተፈቀደላቸው ዓላማ ውጪ ለሌላ ተግባር እንዳያውሉት በማዕድን ቢሮዎች ሆነ በመንገድ ባለሥልጣኖች በኩል ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑን፣ የመንገድ ግንባታቸውን ጨርሰው ቦታውን ለቀው ከመሄዳቸው በፊት በማዕድን አዋጁ መሰረት አካባቢን መልሶ የማቋቋም ስራዎች የማይሰሩ መሆኑ፤ በአጠቃላይ ለመንገድ ግንባታ እና ጥገና ተብሎ በተለየ የሚሰጠውን የኮንስትራክሽን ማዕድን የማምረት/ የመጠቀም ፈቃድ አሰጣጥ፣ ቁጥጥር እና አካባቢን መልሶ የማቋቋም ሥራ እንዲከናወን በቅንጅት የማይከናወን መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

87. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፣ ከክልል የማዕድን ቢሮዎች፣ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ከክልል የገጠር መንገድ ባለሥልጣኖች ጋር የውይይት መድረክ በመፍጥር የመፍትሄ አቅጣጫ ለመዘርጋት እንዳቀዱ ገልፀዋል፡፡

88. በማዕድን ልማት ላይ ለተሰማሩ አካላት ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች አስፈላጊው መፍትሄና እገዛ ማድረግ ካልተቻለ ልማቱን ለማስፋፋትና ሀገሪቷም ከልማቱ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ለማሳደግ ለምታደርገው ጥረት እንቅፋት ይሆናል፡፡ የማዕድን ዘርፉ ላይ ከሚሳተፉ ባለሀብቶች ውጪ ለህዝብ አገልግሎት ለሚውል የማዕድን ሀብት የሚጠቀም አካል የማዕድን ዘርፉን ከሚያስተዳድረው አካል እውቅና ውጪ መጠቀም በሀገሪቷ ውስጥ የሚገኝ የማዕድን ሀብትን የማስተዳደር ስልጣን ያለው አካል ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዳይችል ያደርጋል፡፡

## 2.3 የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ

### የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን በተመለከተ፤

89. የማዕድን ባለፈቃድ በየሳምንቱ የተመረቱትን፣ የተከማቹትን፣ የተዘጋጁትን፣ የተጓጓዙትን፣ ወደ ዉጭ የተላኩትን እና የተሸጡትን ማዕድናት ዝርዝር በመዝገብ ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986 መሰረት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና የማዕድን ባለፈቃዶች በመዝገብ መዝግበው የተያዙትን መረጃዎች ለፍቃድ ሰጪው አካል ሪፖርት የሚያቀርቡበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

የማዕድን ፈቃድ ሰጪው አካል በማዕድን ባለፈቃዶች በየሳምንቱ የተከናወኑ የማዕድን ስራዎችን መረጃ ተደራጅቶ የሚያዝበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግና የፈቃድ አመልካቾች መረጃ በዳታ ቤዝ ተመዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

90. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ለማዕድን አዋጅ 678/2002 አፈጻጸም የሚረዳ ደንብ ተዘጋጅቶ ያልወጣ በመሆኑ የክልል ማዕድን ቢሮዎች/ ኤጀንሲዎች ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ አለመዘጋጀቱ ታውቋል፡፡

91. ስለጉዳዩ የማዕድን ሚኒስቴር ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፣ ረቂቅ የደንብ ዝግጅት ሥራ በመጠናቀቅ ላይ እንደሚገኝ፣ እንደተጠናቀቀ ለሚኒስትሮች ምክር ቀርቦ እንዲጸድቅ እንደሚደረግና መመሪያዎችም ተዘጋጅተው ለክልል ማዕድን ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች የሚላክ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

92. በ2002 ለወጣው ማዕድን አዋጅ ደንብ አለመውጣቱ እና በነባሩ ደንብ እየተጠቀሙ መሆናቸው በአዲሱ አዋጅ የተለወጡ ጉዳዮችን ሥራ ላይ ለማዋል በአስፈጻሚ አካላት በኩል ችግር እንዳስከተለባቸው ገልጸዋል፡፡

**የካዳስተር ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ**

93. የማዕድን ሚነስቴር የማዕድን ፈቃድ መረጃን ለመለዋወጥ የሚረዳ በአገር አቀፍ ደረጃ ሥራ ላይ እንዲውል የካዳስተር ሥርዓት ዘርግቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልሎች ተግባራዊ መደረግ መጀመሩ፣ የደቡብ፣ የኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች የካዳስተር ስርዓቱን በክልል ደረጃ እየተጠቀሙበት የተገኙና ነገር ግን የአዲስ አበባ ከተማና በየክልሎች የሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የማዕድን ፈቃድ በየደረጃው የሚሰጡ አካላት ግን እየተጠቀሙበት አለመሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

94. የማዕድን ሚኒስቴር ማዕድን ፍለጋም ሆነ ማምረት ፈቃድ ሲሰጥ የክልሎችን አስተያየት ሳይጠይቅ ፈቃድ የሚሰጥ በመሆኑ፣ ክልሎች የሚያውቁት በካዳስተር ላይ ቦታው የተያዘ መሆኑ እና በደብዳቤ ብቻ እንደሆነ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የካዳስተር ሥርዓቱ በክልል ደረጃ ብቻ እንጂ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የማዕድን ፈቃድ የሚሰጡ አካላት እንደማይጠቀሙበት ታወቋል፡፡

95. የሚድሮክ የወርቅ ማዕድን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሳካሮ የወርቅ ምርመራ ፈቃድ የነበረው ሲሆን እ.ኤ.አ. በ24/11/2009 የማምረት ፈቃድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ መውሰዱን ነገር ግን የሳካሮ ወርቅ ለማምረት በተሰጠው ፍቃድ ክልል ውስጥ የኦሮሚያ ክልል ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ደግሞ በዛው ይዞታ ውስጥ ለባህላዊ ወርቅ አምራቾች የማምረት

ፈቃድ እየሰጠ መሆኑንና ለሚድሮክ ወርቅ ማዕድን የማምረት ፈቃድ መሰጠቱን መረጃ የሌላቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

96. ስለጉዳዩ የማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ፣ ከካደስተር በፊት በደብዳቤ ይጠየቅ እንደነበር፣ ካደስተሩ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ የደብዳቤ ልውውጡ እንደማያስፈልግ፣ ሆኖም ፈቃድ ከመሠጠቱ በፊት በጋዜጣ እንደሚወጣ እና ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ ደግሞ የፈቃድ ኮፒ ለክልሎች እንደሚላክ፣ በተጨማሪም ሥርዓቱን በዞን እና በወረዳ ደረጃ ለመዘርጋት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ ዞን እና ወረዳዎች የሰጡትን ፈቃድ በሲዲ እየቀዱ ለክልል ማዕድን ቢሮዎች በየሳምንቱ እንዲልኩና ክልሎች ደግሞ ከታች የመጣውን ፈቃድ ሆነ እነርሱ የሰጡትን ፈቃዶች ወደ ካዳስተሩ እንዲያስገቡ ስልጠናና መመሪያ የተሰጠ ቢሆንም ተግባራዊ ባለማድረጋቸው የተፈጠረ ችግር መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

97. በማዕድን ሚኒስቴር የተዘረጋው የካዳስተር ሲስተም ሙሉ ለሙሉ በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ ያለመደረጉ በካዳስተሩ ምክንያት ደብዳቤ መፃፃፍ በመቅረቱ ክልሎችም ካዳስተሩን ባለመጠቀማቸው የማዕድን ቦታዎች በፌደራልም በክልልም ተመሳሳይ ቦታ ላይ ተደራራቢ ፍቃድ የመሰጠት እድሉን ሰፊ ያደርገዋል፡፡

## <u>በባለፈቃዶች መያዝ የሚገባቸውን መረጃዎች በተመለከተ</u>

98. የማዕድን ባለፈቃዶች በየሳምንቱ የተከናወኑ የማዕድን ስራዎችን በስራ ላይ የደረሱ አደጋዎችን የተመለከተ መረጃ መያዝ እና ፈቃድ ለሰጣቸው አካል በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986 መሰረት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

99. ነገር ግን በናሙና ከተመረጡ ባለፍቃዶች እነዚህን መረጃዎች ሁሉም መዝገበው የሚይዙ ሲሆን ነገር ግን በመዝገብ መዝግበው የተያዙትን መረጃዎች ለፍቃድ ሰጪው አካል ሪፖርት የማያደርጉ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

100. ስለጉዳዩ የማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤት ኃላፊዎች በነባራዊ መግለጫ በሰጡት ምላሽ፣ በየሣምንቱ ለሚኒስተር መ/ቤቱ እንዲያቀርቡ እንደማይገደዱ፣ ሆኖም በህጉ መሠረት በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986 መሰረት ፍቃድ ለሰጣቸው አካል በየሳምንቱ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለባቸው ስለሚደነግግ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

101. የማዕድን ባለፈቃዶች የተከናወኑ የማዕድን ስራዎችን መረጃ በአግባቡ መያዝ እና ፈቃድ ለሰጣቸው አካል ያለማቅረባቸው የተከናወኑትን ሥራዎችን ሆነ በዘርፉ የሚደርሱ አደጋዎችን ለማወቅ እና መፍትሔ ለመስጠት ለመከታተል እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ትክክለኛ ገቢ ለማወቅም ሆነ የዘርፉን እንቅስቃሴ ትክክለኛ ገጽታን ማወቅ አይቻልም፡፡

# ክፍል ሦስት፡

## መደምደሚያዎች

102. **የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ በማልማት ስራ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፈቃድ አሰሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፤**

- ለማዕድን አዋጅ 678/2002 አፈጻጸም የሚረዳ ደንብና መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት እና መስፈርት የተዘጋጀ ቢሆንም መስፈርቱን ሳያሟሉ ፈቃድ የተሰጣቸው የማዕድን ባለፈቃዶች መኖራቸው፣
- ለብሔራዊ ፓርክነት እና ለተፈጥሮ ጥብቅ ደን በተከለሉ ሥፍራዎች የማዕድን ፍለጋ እና የማምረት ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ፣
- የምርመራ ፈቃድ ወቅቱን ጠብቆ የማይታደስ ወይም የማይሰረዝ መሆኑ፣
- ማዕድን ለማልማት ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በገቡት ውል መሰረት ስራቸውን የማያከናውኑ ባለፈቃዶች መኖራቸው፣
- የአፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ወቅቱን ጠብቆ የማይቀርቡ እንዲሁም በሚቀርቡት ሪፖርቶች መሰረት የታዩ ክፍተቶች ወይም የተነሱ ችግሮች ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ አፋጣኝ ምላሽ የማይሰጥ መሆኑ፣
- የሮያሊቲ ክፍያ ወቅቱን ጠብቀው የማይፈፅሙ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች መኖራቸው፣ በክልሎች በባህላዊ መንገድ ከሚመረት ወርቅ ሮያሊቲን ለመሰብሰብ የሚያስችል ወጥ የሆነ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያለመደረጉና ሮያሊቲ የማይሰበስቡ ክልሎች መኖራቸው፣
- የመንግስት ነፃ የአክሲዮን ድርሻ በቀድሞው አዋጅ 2% በአዲሱ አዋጅ ደግሞ 5% በፌደራል ደረጃም ሆነ በክልል የማይሰበሰብ መሆኑ፣
- ለማዕድን ልማት ሲባል ከቀረጥ ነፃ የገቡ የተለያዩ መሳሪያዎች ለተባለላቸው አላማ ብቻ እየዋሉ ለመሆኑ ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣

103. **የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎች ለማስወገድና ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፤**

- የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተዘጋጀና ለሚመለከታቸው አካላት ያልተሰራጨ መሆኑ፣

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች ሁሉም የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አቅርበው ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች በፍቃዱ ክልል አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች የተቀናጀ የማህበረሰብ ልማት ዕቅድ የማያዘጋጁና ለዚህም የሚያስፈልግ ወጪ /ፈንድ የማይመድቡ መሆኑ፣ ይህንን ለማስፈጸምም የሚረዳ ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ለማዕድን ሥራ ውለው የነበሩ አካባቢዎችን ልማቱ ሲጠናቀቅ ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ፈንድ ማዕድን ባለፈቃዶች ፈቃድ ሲሰጣቸው በውሉ ላይ ከሚገለጽ የገንዘብ መጠን በስተቀር አብዛኛዎቹ የማይመድቡ መሆኑ፣ ባለፈቃዶች የመደቡት ገንዘብ የት መቀመጥ እንዳለበት እና እንዴት ሥራ ላይ መዋል እንዳለበት እንዲሁም ስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- በማዕድን ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት ደንብና መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተዘጋጀ እና ለሚመለከታቸው የክልል አካላትም ሆነ በመስኩ ለተሰማሩ ድርጅቶች ያልተሰራጨ መሆኑ፣
- የማዕድን ሚኒስቴር ማዕድን ፍለጋም ሆነ ማምረት ፈቃድ ሲሰጥ የክልሎችን አስተያየት ሳይጠይቅ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ፣
- ለመንገድ ግንባታና ጥገና የሚያገለግሉ የኮንስትራክሽን ማዕድናት በህግ በተደነገገው መሰረት በነጻ የሚጠቀሙ መሆኑ ቢታወቅም፣ ለኮንስትራክሽን ማዕድን ሥራ ቦታውን ሲወስዱ የሚኒስቴር መ/ቤቱንም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች/ ኤጀንሲዎች እንዲያውቁ የማይደረግ መሆኑ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚወስዱ፣ ሥራቸውንም ሲያጠናቅቁ መልሶ ለማልማት ፈንድ የማይመድቡ መሆኑ፣

104. ***የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፤***

- የማዕድን ሚነስቴር የማዕድን ፈቃድ መረጃን ለመለዋወጥ የሚረዳ በአገር አቀፍ ደረጃ ሥራ ላይ እንዲውል የተዘረጋው የካዳስተር ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልሎች ተግባራዊ መደረግ የጀመረ ቢሆንም የማይጠቀሙ ክልሎች እንዳሉ እና በየክልሎች የሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣
- የማዕድን ባለፈቃዶች የተከናወኑ የማዕድን ስራዎች በተመለከተ እና የደረሰ ጉዳት ካለ ተገምግሞ መረጃን ለፍቃድ ሰጪው አካል ሪፖርት የማያደርጉ መሆኑ፣

105. በአጠቃላይ በአገሪቱ የማዕድን ልማቱን ለማስፋፋትና በአካባቢና በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት እንዳያስከትል እና ህብረተሰቡም ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሌሎች

የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም ባለሀብቶች ጋር በመቀናጀትና በማስተባበር በርካታ ሥራ መስራቱ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የማዕድን ልማቱን ለማሳደግ፣ በአካባቢ ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተፅዕኖዎች በአግባቡ መተዳደራቸውና የልማት ስራዎች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች የማህበረሰብ ልማት በአግባቡ ሥራ ላይ ካልዋለ እንዲሁም ተግባራዊነቱ የሚያረጋግጥ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ካልተዘረጋ የተጀመረው የማዕድን ልማቱን ለማስፋፋትና ሀገራችን ከልማቱ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚሰራው ሥራ ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ያሻሽላሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት፡

## የማሻሻያ ሀሳቦች

106. **የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ በማልማት ስራ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፤**

- ለማዕድን አዋጅ 678/2002 አፈጻጸም የሚረዳ ደንብ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ተዘጋጅቶና ፀድቆ ለሚመለከታቸው አካላት ተሰራጭቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የፍቃድ አሰጣጥ መስፈርቱን ማሟላታቸው እየተረጋገጠ ፈቃድ መሰጠቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ማዕድን ለማልማት ፈቃድ የተሰጣቸው አካላትም በገቡት ውል መሰረት ስራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑን በፈቃድ ሰጪው አካል ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ የምርመራ ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች የጊዜ ገደባቸውን ሲጨርሱ የሚታደስበት ወይም የሚቋረጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ለብሔራዊ ፓርክነት በተከለሉ ሥፍራዎችና በተፈጥሮ ጥብቅ ደን እና በአለም አቀፍ ደረጃ የተከለሉ ሥፍራዎች አካባቢዎች አካባቢ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በዱር እንስሳቱና በተፈጥሮ አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድር መሆኑ ሳይረጋገጥ ወይም ጠቀሜታው የበለጠ መሆኑ ሳይረጋገጥ ፈቃድ መሰጠት የለበትም፡፡

- የማዕድን ባለፈቃዶች የአፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ እንዲያቀርቡ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው እና በሚቀርቡት ሪፖርቶች ላይ የሚገለጹ ክፍተቶች ወይም የተነሱ ችግሮች ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች የሮያሊቲ ክፍያ ወቅቱን ጠብቀው እንዲፈፅሙ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ በክልሎች በባህላዊ መንገድ ከሚመረት ወርቅ ሮያሊቲን ለመሰብሰብ የሚያስችል ወጥ የሆነ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የመንግስት ነፃ 5% የአክሲዮን ድርሻ በፌዴራል ደረጃም ሆነ በክልሎች ወቅቱን ጠብቆ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

107. **የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎች ለማስወገድና ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፤**

- የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው

አካላት ሊሰራጭ ይገባል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት እንዲያቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡ ጥናቱም ስለትክክለኝነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

- የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች በፍቃዱ ክልል አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች የማህበረሰብ ልማት ዕቅድ ከአካባቢው መስተዳደርና ህብረተሰብ ጋር በመሆን ሊያዘጋጁና ለዚህም የሚያስፈልግ ወጪ /ፈንድ እንዲመድቡ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ፈንድ ማዕድን ባለፈቃዶች እንዲመድቡ ሊደረግና የተመደበው ፈንድ የማዕድን ፈቃድ ሰጪው አካል ዘንድ ወይም በዝግ የሂሳብ አካውንት እንዲቀመጥ ሊደረግ እና ልማቱ ሲጠናቀቅ ለመልሶ ማቋቋሚያ ተግባር ሊውል ይገባል፡፡ በማዕድን ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት ደንብና መመሪያ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያዘጋጅ እና ለሚመለከታቸው የክልል አካላትም ሆነ በመስኩ ለተሰማሩ ድርጅቶች ሊሰራጭ ይገባል፡፡ የማዕድን ሚኒስቴር ማዕድን ፍለጋም ሆነ ማምረት ፈቃድ ሲሰጥ የክልሎችን አስተያየት ሊጠይቅ ይገባል፡፡
- ለመንገድ ግንባታና ጥገና  የኮንስትራክሽን ማዕድን በህግ በተደነገገው መሰረት በነጻ የሚጠቀሙ አካላት የኮንስትራክሽን ማዕድን ቦታውን ሲወስዱ የሚኒስቴር መ/ቤቱንም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች/ ኤጀንሲዎች ሊያውቁት የሚችሉበት ከመቼ እስከመቼ እንደሚጠቀሙ እና ሥራቸውን አጠናቀው ሥፍራውን ሲለቁ ለቦታው የመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ መድበው ሥራ ላይ የሚውልበት ሥርዓትን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

108. **የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፤**

- የማዕድን ሚነስቴር የማዕድን ፈቃድ መረጃን ለመለዋወጥ የሚረዳ ከፍተኛ ወጪ ወጥቶበት  በአገር አቀፍ ደረጃ ሥራ ላይ እንዲውል የተዘረጋው የፍሌክሲ ካዳስተር በሚኒስቴር መ/ቤቱም፣ በክልሎች ብሎም በዞኖችና ወረዳዎች ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሊደረግ እና ተግባራዊነቱ በቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- የማዕድን ባለፈቃዶች የተከናወኑ የማዕድን ስራዎችና የደረሱ አደጋዎችን የሚገልጽ መረጃን ለፍቃድ ሰጪው አካል ሪፖርት የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

109. በአጠቃላይ በሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ልማት ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፍቃድ አሰጣጥ ሂደቱንና ልማቱ የአካባቢንና የህብረተሰቡን ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ ብሄራዊ ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና በዘርፉ የወጡ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ጥናትን መሰረት በማድረግ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግና አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የተጠናከረ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም በማዕድን ዙሪያ የተሰማሩ ባለሀብቶች ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ሚኒስቴር መ/ቤቱን ሙሉ ለሙሉ የማይመለከቱ ቢኖሩ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የማዕድን ሚኒስቴር፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል፣ የዞን እና የወረዳ መ/ቤቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ:- **የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ልማት ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ልማቱ የአካባቢንና የህብረተሰቡን ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን ማረጋገጥ**

ተደራጊው መ/ቤት:- ***የማዕድን ሚኒስቴር***

| የኦዲት ጭብጥ (Issues) | የመገምገሚያ መስፈርት (Evaluative criteria) |
|---|---|
| 1. የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ በማልማት ስራ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ | 1.1 በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ አካላት የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- ስትራተጂክ ዕቅድ 2003-2007ዓ.ም ገፅ-14) |
| | 1.2 ለፈቃድ አሰጣጥ የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- ስትራተጂክ ዕቅድ 2003-2007ዓ.ም ገፅ-14) |
| | 1.3 በማዕድን ሥራ ላይ ለመሰማራት ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል ግልጽ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- ስትራተጂክ ዕቅድ 2003-2007ዓ.ም ገፅ-14) |
| | 1.4 የማዕድን ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የማዕድን ፈቃድ ጠያቂ አስፈላጊዉን የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ብቃት ያለዉ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 52 ንዑ4/ለ) |
| | 1.5 ማዕድን ለማልማት ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት በገቡት ውል መሰረት ስራቸውን ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- ስትራተጂክ ዕቅድ 2003-2007ዓ.ም ገፅ-14) |
| | 1.6 የማዕድን ምርመራ ፍቃድ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ዉስጥ ባለፈቃዱ የምርመራ ስራዉን መጀመር አለበት፡፡<br>(ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 20 ንዑ 2/ሀ) |
| | 1.7 የማዕድን የማምረት ባለፍቃድ ፍቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ዉስጥ የምርት ሥራዉን መጀመር አለበት፡፡<br>(ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 30 ንዑ 2/ሀ) |
| | 1.8 የቅኝት ፈቃድ ፍቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለ18 ወራት ብቻ መሆን አለበት፡፡<br>(ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀፅ 17 ንዑ1) |
| | 1.9 የምርት ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ባለፈቃድ የፍቃድ ዘመኑ ሲጠናቀቅ ወይም ሥራውን ሲያቋርጥ –በተፈጥሮ አካባቢ ላይ፣ በሰው ህይወትና ንብረት እንዲሁም ዕፅዋት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ማናቸውም ቅሪቶችና ግንባታዎችን ሊያስወግድ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 34 ንዑ1/ቸ) |
| | 1.10 የምርመራ ፈቃድ ፍቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለ3 ዓመት ብቻ መሆን አለበት፡፡<br>(ምንጭ፡-አዋጅ 678/2002 አንቀ 19 ንዑ2 |
| | 1.11 የምርመራ ፈቃድ በየአመቱ ሁለት ጊዜ መታደስ አለበት፡፡<br>(ምንጭ፡-አዋጅ 678/2002 አንቀ 19 ንዑ2) |
| | 1.12 የማዕድን ባለፍቃድ ከማምረቻ ቦታ ላይ ከሚያመርተዉ የማዕድን/ናት ምርት በየግዜዉ በመቶኛ እየተሰላ ክፍያ የሚፈፀምበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል<br>ምንጭ፡- የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀ 63 |
| | 1.13 የተዘረጋዉ ስርዓት ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል<br>ምንጭ፡- የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀ63 |
| | 1.14 የምርምር ባለፈቃድ በየአመቱ እና የምርት ባለፈቃድ በየሩብ ዓመቱ የአፈፃፀም ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-28) |
| | 1.15 በሪፖርቱ መሰረት የታዩ ክፍተቶች/ችግሮች ላይ አስፈላጊው የእርምት እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-27) |
| | 1.16 ግዴታቸውን የማይወጡ ባለፈቃዶች ፈቃዱ እንዲሰረዝ የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 52 ንዑ4/መ ) |
| | 1.17 በማዕድን ልማት ለሚሳተፉ አካላት ለልማቱ የሚያግዙ መሳሪያዎች ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር |


| | |
|---|---|
| | ውስጥ የሚያስገቡበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-አዋጅ 678/2002 አንቀ 73 ንዑ 1 |
| | 1.18 ለማዕድን ስራ ከቀረጥ ነፃ የገቡት መሳሪያዎች በትክክል ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-32) |
| | 1.19 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን እሽግ ናሙናዎችን ለምርመራ ወደ ውጪ እንዲላኩ ፈቃድ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-29) |
| | 1.20 የማዕድን ምርመራ ባለፍቃድ የሙከራና ትንተና ለማድረግ ያወጣቸዉንና ያጓጓዛቸዉን የማዕድናት ናሙና ቅጂዎች ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ (ለምን ያህል ጊዜ) (ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 20 ንዑ2/ሐ) |
| | 1.21 የሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ልማት ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የፍቃድ አሰጣጥና አስተዳደር ጥናት BPR ገፅ 27) |
| | 1.22 በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ ማዕድናት አመራረትና ግብይት ህጋዊ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- ስትራተጂክ ዕቅድ 2003-2007ዓ.ም ገፅ-14) |
| | 1.23 በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ ማዕድናትን አመራረትና ግብይትን በተመለከተ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- ስትራተጂክ ዕቅድ 2003-2007ዓ.ም ገፅ-14) |
| | 1.24 በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ለማምረት ለሚንቀሳቀሱ አካላት የስልጠናና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-34) |
| | 1.25 በባህላዊ ማዕድን አምራቾች የሚመረት ወርቅ እና የጌጣጌጥ ማዕድናት ለብሄራዊ ባንክ ገቢ የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-34) |
| | 1.26 የክልሎችን ፍላጎት በመለየት የቴክኒክና የማቴሪያል ድጋፍ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያገኙበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይገባል፡፡ (ከተራ ቁ.1.23 በምን ይለያል) (ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-35) |
| 2. የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎች ለማስወገድና ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፣ | 2.1 የማዕድን ስራዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎችና አያያዛቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል (ምንጭ፡- የማዕድን ፖሊሲ ገፅ 8) |
| | 2.2 የማዕድን ፈቃድ ጠያቂዎች ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሊያቀርቡ ይገባል (ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 60 ንዑ1) |
| | 2.3 በፈቃድ ጠያቂዎች የሚቀርቡ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶች ትክክለኛነት ፈቃድ በሚሰጠው አካል የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ)፡-የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር የአካባቢና የማህበረሰብ ልማት ኮር የስራ ሂደት የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት ነሐሴ 21/2000 ዓ.ም ገፅ-77 |
| | 2.4 የማዕድን ስራዎች በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች በህብረተሰቡና በአካባቢው ላይ ልማቱ ጉዳት እንዳያደርስ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው ጥናት ተግባራዊነት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ)፡-የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር የአካባቢና የማህበረሰብ ልማት ኮር የስራ ሂደት የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት ነሐሴ 21/2000 ዓ.ም ገፅ-77 |
| | 2.5 ህብረተሰቡ ከማዕድን ልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊነቱ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-5) |
| | 2.6 የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በፍቃዱ ክልል አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች የማህበረሰብ ልማት ዕቅድ የሚሳተፍበትና ለዚህም የሚያስፈልግ ወጪ /ፈንድ የሚመድብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡ አዋጅ 678/2002 አንቀፅ 60 ን.አንቀፅ 3) |
| | 2.7 ከአካባቢ ማህበረሰቦች፣ ከማዕድን ስራ ከተሰማሩ ባለሀብቶችና ከክልል መንግስታት ጋር በመተባበር የተቀናጀ የአካባቢ ልማት እቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡የማዕድን ፖሊሲ ገፅ-8) |
| | 2.8 ከማዕድን ባለፍቃዶች በተገኘው ፈንድ ከፈቃድ አካባቢ ላለው ህዝብ የሚሰሩትን የማህበረሰብ ልማት ስራዎችን በመከታተል ሪፖርት የሚቀርብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 60 ንዑ2) |
| | 2.9 ባህላዊ የማዕድን አምራቾች የማዕድን ኤክስቴሽን አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉበት ሥርዓት |

| | |
|---|---|
| | ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡የማዕድን ፖሊሲ ገፅ-8) |
| | 2.10 ለማዕድን ስራ ጤንነትና ደህንነት ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡የማዕድን ፖሊሲ ገፅ-8) |
| | 2.11 የተዘጋጀዉ ደንብና መመሪያ ተግባራዊነት ሊገመገም እና ተግባራዊ በማያደርጉ ላይ ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡የማዕድን ፖሊሲ ገፅ-8) |
| | 2.12 የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማና ለመልሶ ማቋቋሚያ የማዕድን ባለፍቃዶች ፈንድ ሊመድቡ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 60 ) |
| | 2.13 የመልሶ ማቋቋሚያ የሚመደበዉ ፈንድ ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ፡፡<br>(ምንጭ፡- አዋጅ 678/2002 አንቀ 60 ንዑስ አንቀጽ4) |
| 3. የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ | 3.1 ለማዕድን ልማትና ለመሰረተ ልማት–ግንባታዎች ጠቀሚታ ያላቸውን የመሰረታዊ የጂኦሳይንስ መረጃዎች ሊሰበሰቡ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-5) |
| | 3.2 የተሰበሰቡት መረጃዎች ሊደራጁና ሊጠበቁና ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- ስትራተጂክ ዕቅድ 2003-2007ዓ.ም ገፅ-14) |
| | 3.3 መረጃዎቹ ለተጠቃሚዎች የሚደርሱበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-5)<br>(ምንጭ፡- ስትራተጂክ ዕቅድ 2003-2007ዓ.ም ገፅ-14) |
| | 3.4 በማዕድን ዘርፍ የግል ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የፕሮሞሽን ስራዎች ሊከናወኑ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡የማዕድን ፖሊሲ ገፅ-8) |
| | 3.5 የፈቃድ አመልካቾች መረጃ በዳታ ቤዝ ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የ2004ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድና መርሃ ግብር ገፅ-2 |
| | 3.6 ማንኛዉም ባለፍቃድ በየሳምንቱ ጠቅላላ የተከናወኑ የማዕድን ስራዎችን፣ ሠራተኞችን፣ የሥራ ሁኔታዎችን እና አደጋዎችን መዝግቦ ፈቃድ ለሰጠው አካል በተወሰነ ጊዜ ሪፖርት የሚቀርብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የምንስትሮች ም/ቤት ደንብ182/1986 አንቀ 30 ንዑ1 /ሀ/2) |
| | 3.7 የማዕድን ባለፈቃድ በየሳምንቱ የተመረቱትን፣ የተከማቹትን፣ የተዘጋጁትን፣ የተጓጓዙትን፣ ወደ ዉጭ የተላኩትን እና የተሸጡትን ማዕድናት ዝርዝር በመዝገብ ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ182/1986 አንቀ 30 ንዑ1 /ሀ/3)/ |
| | 3.8 የማዕድን ባለፈቃዶች በመዝገብ መዝግበው የተያዙትን መረጃዎች ለፍቃድ ሰጪው አካል በተወሰነ ጊዜ ሪፖርት የሚያቀርቡበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡(ምንጭ፡ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ182/1986 አንቀ 30 ንዑ1 /ሀ/3)) |
| | 3.9 የማዕድን ፈቃድ ሰጪው አካል በማዕድን ባለፈቃዶች የተከናወኑ የማዕድን ስራዎችን መረጃ ተደራጅቶ የሚያዝበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ182/1986 አንቀ 30 ንዑ1 /ሀ/3)) |
| | 3.10 የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ :-ከመልካም ተመክሮ ) |


**አባሪ 2**

## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process discriptions)


**<u>የማዕድን ፍለጋ/ምርመራ ሥራ ፈቃድ የሥራ ፍሰት</u>**




# የማዕድን ምርት ሥራ ፈቃድ የሥራ ፍሰት



## የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት



## የአካባቢ ማህበረሰብ ልማት ዩኒት



## በናሙና የተመረጡ ክልሎችና ወረዳዎች

| ተ.ቁ | የክልሎች ዝርዝር | ከተማ/ወረዳ | የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ አስተዳደር | አዲስ አበባ | በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የማዕድን ኃብት ጥናትና አስተዳደር ቨርዥን የቀረበ ቃለ መጠይቅ |
| | | | በክልሉ ፈቃድ የተሰጡ የፍቃድ ቦታዎችን በአካል መጎብኘት |
| 2 | ኦሮሚያ ብ/ክ/ መንግስት | አዲስ አበባ | ለኦሮሚያ የማዕድን ሀብት ልማት አስተዳደር የስራ ሂደት ባለቤት የቀረበ ቃለመጠይቅ |
| | | ሻኪሶ | በባህላዊ መንገድ የሚመረት ወርቅን በአካል መጎብኘት |
| 3 | ደቡብ ህ/ብ/ክ መንግስት | አዋሳ | ለክልሉ የማዕድን ሀ/ጥ/አስ/የሥራ ሂደት ባለቤት የቀረበ ቃለመጠይቅ |
| | | | በክልሉ ፍቃድ የወሰዱ በአዋሳ ከተማ የሚገኙ ባለፍቃዶችን (DMS፣ ዳኢቴ፣ ድራጎን፣ ሜድሮክ) እና የካኦሊን ምርት በአካል ማየት |
| | | ሀዲያ ዞንሆሳዕና | ለሀዲያ ዞን የውኃ፣ የማዕድንና ኢነርጂ ዋና መምሪያ የቀረበ ቃለመጠይቅ |
| | | | በሀዲያ ዞን ፈቃድ የተሰጣቸው ባህላዊ አምራቾች (አሸዋ፣የአለት) በአካል መጎብኘት |

## በናሙና የተመረጡ በማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ የተሰጣቸውና የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው ባለፈቃዶች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የባለፍቃዶች ዝርዝር | የሚገኙበት ክልል/ወረዳ | የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | የሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃ/የ/የ/ማህበር | በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን በሻኪሶ | የሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ዋና ስራ አስኪያጅ የቀረበ ቃለ መጠይቅ |
| | | | በወርቅ ማምረቻ ቦታው (የለገደንቢና ሳካሮ) በአካል መጎብኘት |
| 2 | አቢጂያታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር | በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን የአዳሚ ቱሉ ጁዶ ኮምቦልቻ ወረዳ | አቢጂያታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር የኦፐሬሽን ስራ አስኪያጅ የቀረበ ቃለመጠይቅ |
| | | | የማምረቻ ቦታውን በአካል መጎብኘት |
| 3 | ኑሪት ጀነራል ቢዝነስ ኃ/የ/የግልኩባንያ | አዲስ አበባ | ለአስተዳደርና ሎጀስቲክ ኃላፊ የቀረበ ቃለመጠይቅ |
| | | | የማምረቻ ቦታውን በአካል ማየት |
| 4 | ጃም ኃ/የ/የ/ ማህበር | አዲስ አበባ | ኦፐሬሽን ሥራ አስኪያጅ Oprational manager |
| | | | የማምረቻ ቦታውን በአካል ማየት |
| 5 | ታርጌት ኢንደስትሪኃ/የ/የግል ማህበር | አዲስ አበባ | ለዋና ስራ አሲኪያጅ የቀረበ መጠይቅ |

## በናሙና ከተመረጡት ባለፈቃዶች ዉስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ማዕድን ለማምረት ፈቃድ ለመስጠት የጠቀመጠውን የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ወይም መስፈርቶች አሟልተው ፈቃድ ስለመሰጠቱ መረጃ ያልቀረበላቸው

| No | Licensee name/ የፈቃድ ስም | ያላሟሏቸዉ መስፈርቶች | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ID card/ passport | Feasibility study | EIA Report | Tax Identification Number {TIN} | Principal business registration certificate | Evidence verifying the financial status of the Applicant | Work program | Not signed by mineral operations Department | Article of Association | Memorandum of Association | Legal form |
| 1) | China Long Hoa Milla Construction Materials P.L.C | X | ✓ | X | X | ✓ | X | ✓ | X | ✓ | ✓ | X |
| 2) | *ETNO Plc.........* | X | X | X | X | X | X | ✓ | X | ✓ | X | X |
| 3) | *JAM Industrial PLC.* | ✓ | X | X | X | ✓ | X | X | X | X | X | X |
| 4) | Ture Dire Dawa Cement Factory Share Company | X | X | X | X | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | ✓ | X |
| 5) | Midroc Gold Mine P.L.C (Lega Dembi) | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 6) | Midroc Gold Mine P.L. C (Sakaro) | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 7) | Daylight Applied Technologies PLC | X | X | X | X | X | X | x | x | x | x | ✓ |
| 8) | Abyssinia Cements Plc | X | x | X | ✓ | ✓ | ✓ | X | X | X | X | X |
| 9) | Target Industries PLC | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | X | X | X | X |
| 10) | Ethio Pack Coal Mining | ✓ | ✓ | X | X | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X |
| 11) | C.G.C Overseas Construction Ethiopia | X | X | X | X | X | X | X | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 12) | Daylight Applied Technologies PLC | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ |
| 13) | Dashen Cement factory PLC | X | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | X | X | X | ✓ | ✓ | X |
| 14) | Three M Marble and Terrazzo Manufacturing Plc | ✓ | ✓ | ✓ | X | X | X | X | X | ✓ | ✓ | X |
| 15) | Abijata Soda Ash S.C | X | X | X | X | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | ✓ | ✓ |
| 16) | Sammakka Stones Plc | ✓ | X | X | X | X | X | ✓ | X | ✓ | ✓ | X |
| **ድምር** | | 9 | 9 | 11 | 11 | 6 | 10 | 7 | 13 | 6 | 7 | 10 |
| 17) | Red Fox International Investment Business Plc | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ |

| No | Licensee name/ የፈቃድ ስም | ያላሟሏቸዉ መስፈርቶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ID card/ passport | Feasibility study | EIA Report | Tax Identification Number {TIN} | Principal business registration certificate | Evidence verifying the financial status of the Applicant | Work program | Not signed by mineral operations Department | Article of Association | Memorandum of Association | Legal form |
| 18) | Stone Fields ConstructionP.L.C | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ | ፋይሉ ያልቀረበ |
| 19) | Nurit General Business PLC | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ |
| 20) | A Zeyneba Mining plc | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ |
| 21) | Bona Ethio-India Marble and Mining Factory Plc | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ | ፎርሙ በፋይል ዉስጥ ያልተያያዘ |

## ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርመራ ፈቃድ ወስደ. እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ፈቃዳቸው በወቅቱ ለማሳደሳቸው ወይም ለመሰረዙ ማስረጃ ያልቀረበላቸው ባለፈቃዶች ዝርዝር

| | Licensee Name | MINERAL_TYPE | LOCALITY | REGION | ISSUE DATE (G-C) | EXPIRY DATE (G-C) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | Sainik Coal Mining P.L.C | Potash | Musley and Crescent Localities | Afar N.R.S | 10/19/2007 | 10/18/2010 |
| 2. | Nova Potash PLC | Potash and Related Salt Minerals | Dallol | Afar N.R.S | 7/9/2008 | 7/8/2011 |
| 3. | G and B Central African Resources Ltd | Potash | Danakil Depression | Afar N.R.S | 8/21/2008 | 8/20/2011 |
| 4. | G and B Central African Resources Ltd | Potash | Danakil Depression | Afar N.R.S | 12/12/2008 | 12/11/2011 |
| 5. | BHP BILLITON WORLD EXPLORATION INC | Potash and Related Salt Minerals | Danakil | Afar N.R.S | 9/2/2009 | 9/1/2012 |
| 6. | Alana potash Afar plc | Potash and Related Salt Minerals | Dallol | Afar N.R.S. | 5/13/2008 | 5/12/2012 |
| 7. | Alana potash Afar Plc | Potash and Related Salt Minerals | Dallol | Afar N.R.S. | 5/13/2008 | 5/12/2012 |
| 8. | Alana potash afar Plc | Potash and Related Salt Minerals | west tendaho and Dallol | Afar N.R.S. | 5/13/2008 | 5/12/2012 |
| 9. | Midroc Gold Mine P.L.C | Precious, Base & Rare Metals | Metekel Zone Baruda-Bulen, Ablarus,Bahu-Anjakoya, Yabanja & West Tangoy | Benishangul Gumuz N.R.S | 3/22/2005 | 3/21/2012 |
| 10. | Ascom Mining Ethiopia Plc | Gold and Base Metals | Shungu and Nazali Localities | Benishangul Gumuz N.R.S | 11/7/2008 | 5/6/2010 |
| 11. | Rayan Investiment PLC | coal | metekel zone,Dibate Werda,Galessa Locality | Benishangul Gumuz N.R.S | 12/19/2008 | 12/18/2011 |
| 12. | Rayan Investiment PLC | Gold, Base Metals, Granite and Marble | Jejebe-Gessa and Geshe | Benishangul Gumuz N.R.S | 1/6/2009 | 1/5/2012 |
| 13. | Sammakka Stones Plc | Marble | Tulu Berkasa | Benishangul Gumuz N.R.S | 7/31/2009 | 7/30/2012 |
| 14. | Zhong E Mining Plc | Precious and Base Metals | | Benishangul Gumuz N.R.S | 9/10/2009 | 9/9/2012 |
| 15. | KRIPTO Mining and Chemicals PLC | Gold And Base Metals | Metekel Zone,Dibate Werda,Korka Locality | Benishangul Gumuz N.R.S. | 8/20/2008 | 8/19/2012 |
| 16. | Rayan Investiment PLC | Gold & Base Metals | Tuski, Gambela and geshe | Benshangul Gumuz N.R.S | 6/22/2007 | 6/21/2010 |

| Licensee Name | MINERAL_TYPE | LOCALITY | REGION | ISSUE DATE (G-C) | EXPIRY DATE (G-C) |
|---|---|---|---|---|---|
| 17. Rayan Investiment PLC | Granite | Bambesi locality, Kamashi Zone | Benshangul Gumuz N.R.S | 6/22/2007 | 6/21/2010 |
| 18. Benzu Gold Mining(Ethiopia)Plc | Gold & Base Metals | Asosa and Kurmuk | Benshangul Gumuz N.R.S. | 1/25/2007 | 1/24/2012 |
| 19. Rayan Investiment PLC | Gold & Base Metals | Oda Godere | Benshangul Gumuz N.R.S. | 9/5/2007 | 9/4/2010 |
| 20. Rayan Investiment PLC | Limestone, Clay and Gypsum | Hurso, Melka Jebdu, Mudi Aneno-Urdada. | Dire Dawa Provisional Administration | 8/3/2007 | 8/2/2010 |
| 21. Rayan Investiment PLC | Clay | Melka Jebdu | Dire Dawa Provisional Administration | 7/3/2009 | 7/2/2012 |
| 22. Abyssinia Cements Plc | Iron Ore | Bidimo Locality, Bale Zone | Oromia N.R.S | 6/30/2006 | 6/29/2009 |
| 23. Abyssinia Cements Plc | Coal | Gojeb (Moye) Locality Jima Zone. | Oromia N.R.S | 6/30/2006 | 6/29/2011 |
| 24. NYOTA MINERALS (ETHIOPIA) LTD | Gold & Platinum-Group Metals | Tulu Kapi & Anchore | Oromia N.R.S | 5/27/2005 | 5/26/2011 |
| 25. NYOTA MINERALS (ETHIOPIA) LTD | Gold and Platinum Group metals | Yubdo | Oromia N.R.S | 6/29/2004 | 6/28/2011 |
| 26. NYOTA MINERALS (ETHIOPIA) LTD | Gold & Platinum-Group Metals | Billa-Gulliso | Oromia N.R.S | 12/20/2006 | 12/19/2010 |
| 27. Gui Family Tantalum-Niobium East Africa Ltd | Tantalum Minerals | Kenticha (Lolotu) | Oromia N.R.S | 12/27/2006 | 12/26/2009 |
| 28. Midroc Gold Mine P.L.C | Precious, Base & Rare Metals | Ula Ulo - Meleka Area | Oromia N.R.S | 3/4/2005 | 3/3/2011 |
| 29. Rayan Investiment PLC | Limestone, Gypsum, Sandstone & Clay | Kola Mojo & Kola Gedera, Around Filklik, North Showa | Oromia N.R.S | 11/24/2006 | 11/23/2009 |
| 30. Derba MIDROC Cement P.L.C | Cement Raw material (limestone,marl,clay,gypsum) | Derba-Mugher | Oromia N.R.S | 4/30/2007 | 4/29/2010 |
| 31. Derba MIDROC Cement P.L.C | pumice | North of Meki town and Southeast of Alemtena | Oromia N.R.S | 6/22/2007 | 6/21/2010 |
| 32. EL Mining PLC | Gold and Associated Minerals | Siyo hawi Welel,Metu Darimu and Gawa | Oromia N.R.S | 2/18/2008 | 2/17/2012 |
| 33. KRIPTO Mining and Chemicals PLC | Gold & Base Metals | Kajimitti-Tulu | Oromia N.R.S | 3/8/2008 | 3/7/2011 |
| 34. Mr. Wang Jingmu | Gold, tantalum and niobium | Kenticha | Oromia N.R.S | 4/2/2008 | 4/1/2011 |
| 35. MYK Cement Industries PTE LTD (Ethiopian Branch) | Limestone, gypsum , sandstone and marl | Halelu Wegidi and Ariro Tere | Oromia N.R.S | 5/8/2008 | 5/7/2011 |
| 36. Dangote Inbdustries | Limestone and Gypsum | Mugher | Oromia N.R.S | 5/27/2008 | 5/26/2012 |

| Licensee Name | MINERAL_TYPE | LOCALITY | REGION | ISSUE DATE (G-C) | EXPIRY DATE (G-C) |
|---|---|---|---|---|---|
| (Ethiopia) PLC | | | | | |
| 37. Nelvo International Minerals and Metals PLC | Limestone and Gypsum | Kersa,Yabeta, Lencha and Gara Boren | Oromia N.R.S | 7/17/2008 | 7/16/2011 |
| 38. KRIPTO Mining and Chemicals PLC | Coal | Dedo, Bidate Bedu, Ofa Gola and Wemba | Oromia N.R.S | 7/17/2008 | 7/16/2012 |
| 39. Three M Marble and Terrazzo Manufacturing Plc | Lime stone | Metarobi wereda, western shoa | Oromia N.R.S | 8/11/2008 | 8/10/2011 |
| 40. Huang Shan Cement Plc | Limestone | Jema Vally Area | Oromia N.R.S | 9/4/2008 | 9/3/2011 |
| 41. Huang Shan Cement Plc | Gypsum | Jema Vally Area | Oromia N.R.S | 9/6/2008 | 9/5/2011 |
| 42. Zhong E Mining PLC | Precious and Base Metals | South of Yubdo | Oromia N.R.S | 11/3/2008 | 11/2/2011 |
| 43. KRIPTO Mining and Chemicals PLC | Nickel,Cromium and Platinium | Kenticha | Oromia N.R.S | 11/25/2008 | 11/24/2011 |
| 44. Rayan Investiment PLC | coal | Kumbabe, Didu, Amuma Yayu Locality | Oromia N.R.S | 12/23/2008 | 12/22/2011 |
| 45. Aroma Mining Plc | Gold ,Platnium& Base Metals | Mendi | Oromia N.R.S | 12/29/2008 | 12/28/2011 |
| 46. Nelvo International Minerals and Metals PLC | Limestone and Gypsum | URGA-ERERI,JELDU DISTRICT | Oromia N.R.S | 12/29/2008 | 12/28/2011 |
| 47. C.G.C Overseas Construction Ethiopia | Precious & Rare Metals | adola area | Oromia N.R.S | 2/18/2009 | 2/17/2012 |
| 48. Rayan Investiment PLC | Limestone and Clay | Filkilik | Oromia N.R.S | 2/2/2009 | 1/2/2012 |
| 49. Rayan Investiment PLC | pumice | Dady,Goria and Fila | Oromia N.R.S | 1/5/2009 | 1/4/2012 |
| 50. Rayan Investiment PLC | Clay | Goha Tsion | Oromia N.R.S | 6/19/2009 | 6/18/2012 |
| 51. Gui Family Tantalum-Niobium East Africa Ltd | Gold & Associated Minerals | Adola | Oromia N.R.S | 6/25/2009 | 6/24/2012 |
| 52. Red Fox Mining Plc | Gold and Associated Minerals | Denbobi Robele & Anole Gusa | Oromia N.R.S | 4/4/2009 | 4/3/2012 |
| 53. Aroma Mining Plc | Gold ,Platnium& Base Metals | Dale Lalo Wereda, WesternWellega | Oromia N.R.S | 5/11/2009 | 5/10/2012 |
| 54. C.H.CLINKER MANUFACTURER PLC | Limestone | Gebre Guracha | Oromia N.R.S | 7/1/2009 | 6/30/2012 |
| 55. Gui Family Tantalum-Niobium East Africa Ltd | Tantalum and Niobium | Bomba Woha and Kentica | Oromia N.R.S | 7/7/2009 | 7/6/2012 |
| 56. C.G.C Overseas Construction Ethiopia | Gypsum | Muger | Oromia N.R.S | 7/23/2009 | 7/22/2012 |
| 57. C.G.C Overseas Construction Ethiopia | Clay | Muger | Oromia N.R.S | 7/23/2009 | 7/22/2012 |
| 58. C.G.C Overseas Construction Ethiopia | Limestone | Muger | Oromia N.R.S | 7/23/2009 | 7/22/2012 |
| 59. Midroc Gold Mine P.L.C | Gold & Associated Minerals | Lega Dembi, Borena Zone | Oromia N.R.S | 3/29/1998 | 3/28/2001 |
| 60. National Mining Corporation | Gold | Dawa-Digati Area Oda- | Oromia N.R.S | 3/4/1996 | 6/25/2007 |

| Licensee Name | MINERAL_TYPE | LOCALITY | REGION | ISSUE DATE (G-C) | EXPIRY DATE (G-C) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | Shakisso Wereda | | | |
| 61. Zhong E Mining Plc | Precious and Base Metals | | Oromia N.R.S & SNNPRS | 9/10/2009 | 9/9/2012 |
| 62. Teranter General Business (TGB) PLC | Precious and Base Metals | Yedi, Gejo and Seri Qararu | Oromia N.R.S. | 8/19/2009 | 8/18/2012 |
| 63. MRD Australia Mining and Construction Plc | pumice | Koka | Oromia N.R.S. | 7/11/2011 | 7/10/2011 |
| 64. Khanij Resources DMCC | Tantalum, Niobium Beryllium and other associated elements | Hurbukesa | Oromia N.R.S. | 5/27/2009 | 5/26/2012 |
| 65. Metico Mining Plc | Gold & Base Metals | Kiltu kara (Nejo) | Oromia N.R.S. and Benishangul | 5/12/2008 | 5/11/2011 |
| 66. Stella Trading and Industry PLC | Precious and Base Metals | Godera and Guraferda areas | SNNPRS & GPNRS | 8/23/2007 | 8/22/2010 |
| 67. Rayan Investiment PLC | Gypsum | Adalye Babur Tabiya and Dewele Localities,Shinile Zone | Somali N.R.S. | 12/22/2008 | 12/21/2011 |
| 68. MGM Gold Mines PLC | Gold | Haramsam and Hasamite | Somalia N.R.S. | 11/14/2006 | 11/13/2010 |
| 69. Aberdeen International Inc. | Precious and Base Metals | Menghi, Dul , Agusha Gumu. Axum. | Tigray N.R.S | 1/25/2007 | 1/24/2011 |
| 70. Sheba Exploration Ltd. | Gold & Base Metals | Shehagne Locality | Tigray N.R.S. | 9/22/2006 | 9/21/2011 |
| 71. Harvest Mining P.L.C | Gold & Base Metals | Terakemti, Nefasit, Hamlo, Igub, Adi-Nebrid | Tigray N.R.S. | 4/20/2007 | 4/19/2010 |
| 72. Makeda Mining P.L.C | Gold & Base Metals | Terer , Adi-Gabat | Tigray N.R.S. | 4/20/2007 | 4/19/2010 |
| 73. Aberdeen International Inc. | Precious and base metals | West Shire | Tigray N.R.S. | 11/14/2007 | 11/13/2010 |
| 74. United Mining P.L.C | Precious and Base Metals | Adi Desta | Tigray N.R.S. | 12/3/2007 | 12/2/2010 |
| 75. United Mining P.L.C | Precious and Base Metals | Abereha Atsebeha | Tigray N.R.S. | 4/30/2008 | 4/29/2011 |
| 76. United Mining P.L.C | Precious and Base Metals | Bala | Tigray N.R.S. | 11/6/2008 | 11/5/2011 |
| 77. Harvest Mining P.L.C | Precious & Base Metals | Midre-felasi | Tigray N.R.S. | 12/18/2008 | 12/17/2011 |
| 78. Donia Mining P.L.C | Gold & Base Metals | Atsebi | Tigray N.R.S. | 6/26/2009 | 6/25/2012 |
| 79. SHINY MINING PLC | Precious and Base Metals | Chila | Tigray N.R.S. | 9/7/2009 | 9/6/2012 |
| 80. National Mining Corporation | Gold & Associated Minerals | Chini & Work Amba Area | Tigray N.R.S. | 12/4/1997 | |
| 81. Sheba Exploration Ltd. | Gold and Associated Minerals | Mereto Locality | Tigray N.R.S. | 4/21/2000 | 4/20/2007 |